# ገድል ወይስ ገደል ?




በመምህር ጌታቸው ( ስመ ጥምቀቱ ገብረ ኢየሱስ )

1995 ዓ.ም
አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ

## ምሥጋና

መጽሐፉን በማዘጋጅበትና እዚህ እስከደረስኩበት ጊዜ ሁሉ በሐሳብ ፤ በምክርና በጸሎት ከጎኔ ላልተለየችኝ ባለቤቴ እንዲሁም መጽሐፉን በማረምና በማስተካከል ለረዱኝ ለመምህር ሙሉጌታ ፤ ለየኔታ ልሣነ ወርቅ ፤ ለሊቀ ትጉሃን ጥበበ ወልድና ለመምህር ጌትነት እንዲሁም መጽሐፉን በኮምፒውተር ጽሕፈት ለተባበረችኝ ለወ/ሮ ዓይናለም የከበረ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ።

ማሳሰቢያ :

የቃል አገባብና የሆሄያትን ግድፈት በመታገስ ዋናውን መልእክት እንድትረዱልኝ በታላቅ ትህትና አሳስባለሁ።

**« የሆነው ሁሉ ግን በእግዚአብሔር ነው ክብሩም ለራሱ ብቻ ነው »**

« ገድል ወይስ ገደል » መጽሐፍ
የመጀመሪያ ዕትም ሰኔ 1995 ዓ.ም
ሁለተኛ ዕትም ነሐሴ 1995 ዓ.ም
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ይህች መጽሐፍ መታሰቢያነቷ: ስለከበረው የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ምክንያት በመናፍቃን ተሰደው ለሚገኙና በክፉዎች ትምህርት ተጠልፎ የወደቀው የቤተክርስቲያናችን ምዕመን : በእግዚ አብሔር ክንድ ነጻ ወጥቶ :ሀገራችን ኢትዮጵያም ካለችበት ድህነትና ርግማን ተላቃ : ለከበረው የክርስቶስ ወንጌል የታዘዘች ሆና : የተነገረላትም የተስፋ ቃል ተፈጽሞ : የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚያውጁ መልእክተኞች ( ልዑካን ) የሚፈልቁባት ቡርክት ምድር ሆና ለማየት ሌትና ቀን በልዑል እግዚአብሔር ፊት በእንባ እየተጉ ለሚገኙ እውነተኛ ክርስቲያኖች ትሁን ።

# መክሥተ አርእስት

**ርዕስ** **ገጽ**


1. መግቢያ ———————————— 1
2. ምዕራፍ አንድ ( መጽሐፈ ዜቅ ወመዝሙር )———————— 24
   = መርቆሬዎስ እግዚአብሔርን የተካ ፈጣሪ
   = ስለሰዎች ፍቅር የተሰቀለው
   = ኑ እንስገድላት
3. ምዕራፍ ሁለት ( ገድለ ተክለ ሃይማኖት ) ———————— 37
   = ተክለ ሃይማኖት የነፍሳችን መዳኛ
   = የተክለ ሃይማኖት ልደትና አስተዳደግ
   = የዳዊት መንግሥት በዶሮ ጭንቅላት
   = የይኩኖ አምላክ ንግሥና ( በዶሮ )
   = ዘርዓ ያዕቆብ
   = ወደ መግሥተ ሰማያት የይለፍ ፈቃድ
   = 10 ትውልድ በዝክረ ተክለሃይማኖት .
   = የመቃብሩን ሥፍራ የተሳለመ ይጸድቃል
   = ፍርፋሪ የበላ ይጸድቃል
   = የተክለ ሃይማኖት ተቅማጥ
   = የሸዋ ሰው የመዳን ተስፋው
   = የሙታን መንፈስ ግንኙነት
   = አጥንቱንና ሥጋየን ዳሱት
   = የተዋጀነው በተክለ ሃይማኖት ደም
4. ምዕራፍ ሦስት ( ገድለ ገ/መንፈስ ቅዱስ ) ———————— 71
   = ገብረ መንፈስ ቅዱስ
   = ጣኦት አምላኪው ገነት ገባ
   = ተአምሩ ጽንስ አስወረደ
   = ክርስትና ፡ ክር ( ማተብ ) አይደለም
   = ፈውስ በጠላ ጋን
5. ምዕራፍ አራት ( ተአምረ ማርያም ) ———————— 89
   = የእግዚአብሔር ባሪያ መሆን አያስፈልገንም
   = ሐዋርያው ጳውሎስን በደማስቆ የጠራችው
6. ምዕራፍ አምስት ( ሌሎች መጻሕፍት ) ————————104
   = አብ በከንቱ ደከመ
   = ሚስቱ መበለት ትሁን
   = ለመስቀልና ለማሪያም የሥላሴ ክብር ይገባቸዋል.
   = የተአምርህን መጽሐፍ ሽፋን የተሳለመ

# መግቢያ

በብጹዓን ሊቃነ ጳጳሳት የምትመራ፣ ከ400.000 በላይ አገልጋዮች ያሏት፣ በ35.000 አጣቢያዎች ተከፍላ ቁጥሩ 40.000.000 የሚደርስ ተከታይ ያላትና በሁሉም ያገሪቱ ክልሎች የተዘረጋችዋ ቤተክርስቲያናችን በ4ኛው ክፍለ ዘመን በትውልዱ ሶርያዊ በሆነው በወቅቱ የእስክንድርያ ጳጳስ ከነበረው ከአትናቴዎስ እጅ የአገልግሎት ሥልጣንና ኃላፊነት ተቀብሎ በመጣው በፍሬምናጦስ ( የመጀመሪያው የሃገራችን ጳጳስ ) በኋላም በወንጌል አገልግሎቱ አባ ሰላማ (<u>የሰላም አባት</u>) ከሣቴ ብርሃን ( ብርሃን ገላጭ) እየተባለ በተጠራው ሊቀ ጳጳስ አመካኝነት ክርስትናን ተቀብላ ብሔራዊ ሃይማኖት አድርጋ የኖረች ቤተክርስቲያን (ሀገር) ናት ::

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በባህል፣ በቅርስ፣ የግሏ በሆነ የሥነ-ጽሑፍ፣የፊደል እንዲሁም በሌሎች ዓለማት የማይገኙ የአምልኮ ሥርዓትና መሣሪያዎች ባለቤት የሆነች ታላቅና ጠንካራ መዋቅር ያላት ቤተክርስቲያን ናት

❶ ጀማሪዋ ( ከሣቴ ብርሃን ) በወቅቱ ዓለም አቀፍ ተቀባይነትና ዕውቅና ከነበረው ከአባ አትናቴዎስ መማሩና መሾሙ

❷ የተቀበለቻቸው የሃይማኖት ውሳኔዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆናቸው ( ጸሎተ ሃይማኖት )

❸ በመጽሐፍ ብቻ ተቀምጠው ያሉት ትክክለኛ የሆኑት የነገረ መለኮት ትምህርቶቿ(ትምህርተ ሥላሴ ያልተበረዘው የሥጋዌ ትምህርቷ)

❹ ዛሬ የተመሠረቱበትን ዓላማ ቢለቁም ከልደቱ እስከ ዕርገቱ የሚያሳዩ ስዕላት በቤተክርስቲያን መገኘታቸውና የተጀመሩበት ዓላማ ታሪክ

❺ የቤተክርስቲያን ምሥጢራት እየተባሉ የሚጠሩት ( ጥምቀትና ቁርባን) መልካቸው መገኘቱ ( ዛሬ ዓላማቸውና ትርጉማቸው ቢዛባም) ወ.ዘ.ተ የቤተክርስቲያኒቱን ጥንተ አመሠራረት ወንጌላዊት የነበረች ለመሆኑ ምሥክር ናቸው፡

## የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ለሀገራችን ያበረከተቻው አስተዋጽኦ

1. ቋንቋን ከነፊደሉ በማዘጋጀትና ለባለ ቋንቋዎች ፊደልን መሥራት
2. መንፈሳዊና ሥጋዊውን አስተዳደር በመቅረጽ ሕዝብ የሚተዳደርበት ሕግ መስጠቷ

3. ሀገሪቱ እንደሌሎች የአፍሪካ አሕጉራት በእስልምና እንዳትወሰድ መከላከል
4. ወራሪዎችን ለመከላከል ሕዝብን ማስተባበር
5. ማሕበራዊ ኑሮን መመሥረት ( ጽዋ እድር ማሕበር ወ.ዘ.ተ )
6. የሀገሪቱ የታሪክና የቅርስ ባለቤትና ግምጃ ቤት መሆን
7. እግዚአብሔር በምድራችን ስሙ እንዲጠራና በሕዝቡ ውስጥ ያሠረጸችው ፈሪኃ እግዚአብሔር
8. በሃገሪቱ የሥነ ጽሁፍ እድገት እንዲመጣ ማድረግ ጥቂቶቹ ናቸው::

## የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን የገጠሟት ችግሮች

① ከመጀመሪያው የቤተክርስቲያኒቱ ጳጳስ « አባ ሰላማ » ሞት በኋላ በቋንቋ ፣በባህልና በሥርዓት እንግዳ የሆኑ ለ 1600 ዓመት ያህል በቤተክርስቲያኒቱ ላይ የተሾሙ ጳጳሳት ከቡራኬ በስተቀር ለወንጌል አገልግሎት ትኩረት አለመስጠት ::

② በተለያዩ ምክንያቶችና ዓመታት ወደ ኢትዮጵያ የፈለሱት ነገዶችይዘውት የመጡት የእምነትና የሥርአት ተጽዕኖዎች፣ምሳሌ (አይሁዳውያን ዓረባውያን )

③ የተስዓቱ ቅዱሳን /የ9ኙ ቅዱሳን/ መምጣትና ምንኩስናን የጽድቅ መንገድ አድርገው ማስተማራቸው

④ የዮዲት ጉዲት ወረራና የ40 ዓመት ግዛቷ የፈጠረው የመጻሕፍት መቃጠልና የመምህራን እልቂት እንዲሁም የይሁዲነት ባሕል መስፋፋት

⑤ ነገሥታት ለቤተክርስቲያኒቱ አገልጋዮች ልዩ ልዩ ስጦታ በመስጠት በቤተክርስቲያን ሥፍራን መያዝ ( ሲሶ መንግሥት መሰጠቷ )

⑥ የግራኝ መሐመድ ወረራ ያስከተለው የሊቃውንት ጭፍጭፋ የአብያተ ክርስቲያናት ውድመትና የፈጠረው ክፍተት ፣

⑦ የስህተት መጻሕፍት በገፍ እየተጻፉ ያለ እርምት የወደሙትን ለመተካት ሲባል ወደ ቤተክርስቲያኒቱ እንዲገቡ መደረጉ

⑧ ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ብሔራዊ ሃይማኖት ሆኖ የታወጀው የካቶሊክ እምነት ያስገባው እንግዳ ትምህርትና ባህል

⑩ ወደ ሀገራችን የገቡ ሚሲዮናውያን ወደሃገራችን ሲገቡ ወንጌል ብቻ ሳይሆን የራሳቸውን ልማድ ባሕልና ወግ እንዲሁም ሥርዓት ይዘው በመግባታቸው ለሀገራችን ሕዝብ ስለሃይማኖት የፈጠረበት ግርታ

⑨ በየዘመናቱ የተነሡና አሁንም ያሉት የስህተት አስተማሪዎችና ድርጅቶቻቸው የሚነዙት የክህደት ትምህርት በሀገሪቱ ክርስትና ላይ ያስከተለው ፍርሃት

10 በቤተክርስቲያኒቱ ተጠልለው የሚገኙና የተሰወረ ዓላማቸውን ለመስፈጸም የሚታገሉ ቡድኖች የፈጠሩት የስም ማጥፋት ዘመቻ የፈጠረው ጥርጥር

11 አብዛኛው የቤተክርስቲያኒቱ ምዕመን ለመጽሐፍ ቅዱስ እንግዳና ባዕድ መሆን ቤተክርስቲያኒቱ ከጥንት ጀምሮ ዓላማዋን እንዳታከናውን እንቅፋቶች ሆነውባታል።

አስቀድማ ዓለም ክርስቶስንና የክርስቶስ የሆኑትን ሁሉ እየተቃወመ በወህኒ ሲያስር ሲያሳድድና ሲገድል እንደዛሬው ክፉ ትውልድ ዘር፣ ጎሣና ነገድ ቋንቋ ባሕል ሳያግዳት በፈቃዷ በትውልዱ ሶርያዊ የነበረውን ሰው ወደ እስክንድርያ በመላክ ክርስቶስንና ለድኅነት የሆነውን ንጹህ ወንጌል ተቀብላ ስትሰብክ የነበረቺው ቤተክርስቲያን ከላይ በጥቂቱ በተዘረዘሩትና በሌሎችም ምክንያቶች ዛሬ ለምትገኝበት ውድቀትና ውርደት ተዳርጋለች።

ልዩ ልዩ ነገዶች ወደ ሀገራችን ሲፈልሱ ይዘውት የመጡት ባህልና ወግ ፣/በተለያዩ ዘመናት / የዮዲት ወረራና የ 40 ዓመት ግዛቷ ያስከተለው የሊቃውንት እልቂት ፣ የመጻሕፍትና የቅርሳ ቅርስ ውድመት / 9ኛው መቶ ክፍለ ዘመን / ፣ በየዘመናቱ የተነሱ የሀገራችን ነገሥታት ለአገዛዝ እንዲያመቻቸው ቤተክርስቲያኒቱን በስጦታና በሲሶ መንግሥት (መሬት) ችሮታ እጃቸውን በመንፈሳዊው ጉዳይ ማስገባታቸው ። / ከ1270 - 1974 / ፣ የዘርዓ ያዕቆብ እንቅስቃሴ መነሣት / 1434 - 1468/ የግራኝ አህመድ ወረራ የፈጠረው የመምህራንና የቀሳውስት ጭፍጨፋ / ከ1524 - 1543 / ፣ ለጥቂት ጊዜም ቢሆን በሀገራችን ብሔራዊ ሃይማኖት ሆኖ የታወጀው የካቶሊክ እምነት አስከትሎት የነበረው የመጻሕፍት መቆነጻጸልና መከላለስ / 1626 - 1632 / በልዩ ልዩ ዓመታት ወደ ሀገራችን የገቡት ሚሲዮናውያን ከወንጌል ጋር ይዘውት የመጡትና ያስገቡት ባዕድ ባህልና ወግ ፣እንዲሁም ለ17 ዓመታት በሀገራችን ሰፍኖ የነበረው የሶሺያሊዝም ፍልስፍና/ከ1666- 1983 / ወ.ዘ.ተ በጥንታዊቷና በባለ ታሪኳ ቤተክርስቲያናችን የወንጌል አገልግሎት ላይ በቀላሉ ሊነቀሉ የማይችሉ ችግሮችን ተክለውባት አልፈዋል።

በተለይ የዮዲትና የግራኝ አህመድ ወረራ ያስከተሉት የመጻሕፍትና የሊቃውንት እልቂት በርካታ ልበ ወለድና የተረት መጻሕፍት ባልተማሩና መናፍስታዊ ተልዕኮ በነበራቸው ሰዎች እየተደረሱ ወደ ቤተክርስቲያን ያለከልካይ እንዲገቡና በክርስቶስ ቤተክርስቲያን ላይ ራሳቸውን ሾመው የመንግሥተ ሰማያት በር ዘጊና ከፋች ነን በማለት እስከዛሬ ድረስ የወንጌልን ቦታ እንደተኩ ይገኛሉ።

እነዚህንና የመሳሰሉትን በቅዱሳን ስምና አንዳንዴም የእግዚአብሔርን ስም በተደራቢነት በመጥቀስ ራሳቸውን ሰውረው የሚገኙትን ድርሰቶች ከተሰቀሉበት የከፍታ ስፍራ ወርደው ቦታውን ለከበረው የጌታችን ወንጌል እንዲለቁ ቤተክርስቲያናችንም በጉዳዩ ነቅታ ወደቀደመው የወንጌል አገልግሎት ክብር እንድትመለስ የሚል ጥያቄን የያዘ ጉዳይ ከቅርብ ጊዚያት ወዲህ እየጎላና እየደመቀ መጥቷል።

ይህም ጉዳይ ሰፊ ቁጥር ባለው ወጣትና በአንዳንድ የቤተክርስቲያኒቱ አገልጋዮች መካከል አለመግባባትን ፈጥሯል። በአጭር ጊዜ በሁሉም የቤተክርስቲያናችን አጥቢያዎች የተቀጣጠለውና በልዩ ልዩ ምክንያቶች የገቡትን የመናፍቃን መጻሕፍትና፣ ትምህርቶች የይታረሙ ጥያቄ የችግሩን መፈጠር የሚፈልጉ ጥቂት ሰዎች እንደሚሉት እንግዳና አዲስ እንዲሁም ጴንጤዎች ወይም ፕሮቴስታንቶች እያልን የምንጠራቸው ድርጅቶች የፈጠሩት ጥያቄ ሳይሆን ሚሲዮናዉያን ወደ ሀገራችን ከመግባታቸው በፊትና በአውሮፓ የፕሮቴስታንት ጀማሪ ነው የሚባለው ማርቲን ሉተር ሳይነሣ በ15 ኛው ክፍለ ዘመን በነበሩትና እግዚአብሔር በቤተክርስቲያናችን የገባባትን ስሕተት እንድታርም በጊዜው አስነስቷቸው በነበሩት መነኩሴ በአባ እስጢፋኖስና በተከታዮቻቸው የተጀመረ ነው።

ዛሬ የተፈጠረውን ችግር በረጋና ብስለት ባለው ክርስቲያናዊ መልኩ እንዲፈታ ጥረት ማድረግን ይጠይቃል። ምክንያቱም የአሁኑ ጥያቄ ሰፊ ቁጥር ባለው የቤተክርስቲያኒቱ ምዕመን ኅሊና ውስጥ ሥር የሰደደና የተብላላ በመሆኑ በማውገዝና በማሳደድ የሚፈታ አይደለም ።ችግሩ የሁለቱም ወገኖች ብስለት የሚያስፈልገውና ጥንቃቄ የሚያሻው ጉዳይ ነው ።

ትናንት በወጣቶች ላይ ያነጣጠረው ጣታቸው ዛሬ ደግሞ አንቱ የተባሉትን መተኪያም የሌላቸውን መምህራንና ሊቃውንት ጴንጤ · ተሐድሶ ሆነዋል ወይም ይደግፋሉ በማለት ሕዝብ በማሳደም ከጉባኤና

ከመቅደስ እያሳገዷቸው ነው ። ስንት መምህራንና ሊቃውንት ከወንጌል አገልግሎት ታግደው በቤታቸው ውለዋል ፣ ? ።

ወጣቶቹ ይዘዋቸው የተነሱት ጥያቄዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ሳይመረመሩ ዝም ብሎ ጸረ-ማርያም ፀረ-ቤተክርስቲያን እያሉ ከማውገዝ ጥያቄያቸው ይምጣ፣ መምህራን ይዩት በማለት የተናገሩ ሁሉ በተለጣፊ ስሞች እየተቀቡ ይጣላሉ ።

እነዚህ ቤተክርስቲያናችንን ለከፋ ችግር ለመዳረግ ታጥቀው የተነሱ በመሆናቸው ብፁዓን ጳጳሳትን ሳይቀር ተሐድሶ ናቸው በማለት አባቶችን ከምዕመናን ጋር ለማጋጨት ብሎም መረጋጋትም እንዳይኖር ለማድረግ እየተንቀሳቀሱ ነው ።

በእነዚህ ስም ለጣፊዎች ቅጽረ ቤተክርስቲያን እንዳይገቡ የታገዱት ሰዎች ቁጥር የቤተክርስቲያናችንን የወደፊት ዕጣ እጅግ አሳሳቢ ወደ ሆነ ደረጃ ያደርሰዋል።

በየአካባቢያችን አያሌ የወጣት ማኅበራት በስም አጥፊዎች ሴራ ተበትነዋል ። ወጣቶቹ ቤተክርስቲያናችን በማለት የደረሰባቸውን ሁሉ በመታገስ ለመማማር ቢሞክሩም ችግር ለመፍጠር ታጥቀው በተነሱት ጥቂት ሰዎች ተደብድበውና ተፈነካክተው ከቅጽረ ቤተክርስቲያን እንዲባረሩ ተደርጓል ።

«አንድ ስሕተት ተፈጥሯል ጥያቄያችን በትክክል ለብፁዓን አባቶቻችን አልደረሰም ቢደርስ እንኳ በግርግር ፈጣሪዎች ምክንያት አልተረዱልንም ብለን እንገምታለን።

የወጣቶቹ ጥያቄ ጳጳሳትን ሽሮ ሌላ ጳጳስ ይሾም ፣ ቀሳውስትና ዲያቆናት ወይም መነኮሳት አያስፈልጉም አልነበረም ። ቤተክርስቲያናችንም ሙሉ ወንጌል ፣ መካነ ኢየሱስ፣ ወ.ዚ.ተ ትሁን ፣የተዋበው ድንቅ ባሕላችን በእንግዳውና በውጭ ዓለማት ባሕል ይለወጥ የሚል ሃሳብ የያዘ አይደለም።

ክፉዎች ግን ለተሰወረ ዓላማቸው እንዲያመቻቸው አድርገው በሐሰት በጋዜጣቸው፣ በመጽሔታቸው ፣ በአገኙት የክርስቶስ ወንጌል አውደ ምሕረት ላይ ሕዝቡም ሆኑ የተከበሩት የቤተክርስቲያኒቱ ውሳኔ ሰጪ አካላት ብጹዓን ሊቃነ ጳጳሳት የወጣቱን እውነተኛ ጥያቄ አቅጣጫ በማዞር እግዚኦ በሉ :ተሃድሶ የሚባል ጭራቅ :ልዩ ፍጡር መጣ በማለት ወደ ሕዝቡ ሲደርሱ ጸረ ማሪያሞች፥ ወደቀሳውስት ሲደርሱ ቀሳውስት የማይወዱ፥ ወደ ጳጳሳት ሲጠጉ ቤተክርስቲያናችን በፓስተር ትመራ፥ ወደ መጠጥና ጭፈራ ቤቶች ባለቤቶች

ሲደርሱ መጠጥ የሚቃወሙ ወ.ዘ.ተ በማለት ለዓላማቸው መልካሙን ጥያቄ ያጣምሙታል::

ትልቁና የሕዝቡን ጆሮ ሰጥቷቸው ያለው የፈጠራ ድርሰታቸው ሃይማኖት ይታደስ ይላሉ በማለት ሕዝቡን በማወናበድ ላይ ናቸው ሃይማኖት እንዴት ይታደሳል ? / ሰው ሰራሽ ካልሆነ በስተቀር / የክርስትና ሃይማኖት ደግሞ በጌታችን ሞት የተመሠረተች ፣ በሐዋርያት አባቶቻችን የተሰበከች በደጋግ አባቶቻችን የተላለፈች በእግዚአብሔር ፈቃድ የሆነች ናት ::

ታዲያ እግዚአብሔርን ማን ሊያርመው ይችላል? የዚህ ትውልድ ሆነ በቤተክርስቲያኒቱ ያሉ ደጋግ የወንጌል መምህራን ዋና ጥያቄ : በየዘመናቱ ወደ ቤተክርስቲያናችን የገቡና የክርስቶስን ወንጌል ቦታ የያዙ ሁሉ: ቦታውን ለከበረው ወንጌል ይልቀቁ የሚል ነው :: አንድ ምሳሌ እንውሰድ መዳን የሚገኘው ክርስቶስን በማመን ነው ብለው ሐዋርያቱ የሰበኳትን ሃይማኖት አንዳንድ ሰዎች ገብተው መገረዝን ካልጨመራችሁ አትድኑም በማለት በተወደደችው ሃይማኖት ላይ የጨመሩትን በመቃወም መገረዝ እንዲሻር ደብዳቤ ጽፈው ይህን የክርስቶስን ሕግ የሚቃወሙ ግን ከፈለጉ ራሳቸውን ይቆረጡ እንጂ ግዝረትስ ከደኅንነት ጋር አይያያዝም አይጠቅምም በማለት ተቃውመዋል::/ ገላ 5: 2 - 11 የሐዋ 15: 22-29 /አሁን ሐዋርያት ሃይማኖት አዳሾች ናቸውን ? ሊባሉስ ይችላሉን ? በፍጹም ይልቁንም ሃይማኖታቸውን ከብክለት ጠበቁ እንጂ:: የወቅቱ የቤተክርስቲያናችን ጥያቄ ይህንኑ ነው:: ሃይማኖት እንዴት የታደሳል ? በሃይማኖታችን ላይ የተደረተ ሁሉ ግን መታደስ አይደለም መፍረስ ሲያንሰው ነው:: አንዳንዶችን ያታለሉበትና የዓላማቸው ማስፈጸሚያ የሆናቸው ዘዴም ቤተክርስቲያናችን ፈጽሞ ስህተት የሌለባት የነጻች እንከን አልባ እንዲያውም መላእክት እንኳ የሚያመልኩባት ናት በማለት የታሪካችንን እና የዕድሜያችንን ርዝማኔ እንደመጋረጃ በመጠቀም የሚያናፍሱት ወሬ ነው::

ነገሩ ያልገባቸው አልያም ለቤተክርስቲያንችን ውደቀት ሆን ብለው የተነሱ ካልሆነም የዋህነታቸው እንደመጽሐፍ ቅዱስ ያልሆነ ሰዎች እንደሚሉት የትውልዱ ጥያቄ ዓላማ ቤተክርስቲያንን የሚያፈርስ፣ ሃይማኖትን የሚያፋልስ፣ ሃገር የሚቆርስ፣ የጌታችንን እናት ቅድስት ድንግል ማርያምን የሚጠላ፣ ክርስቶስን ፍጡር፣ ሰጋጅ፣ አድርጎ የሚያስተምር እንዲሁም ለወንጌል ክብር፣

ስለ ክርስቶስም ስም መከራ የተቀበሉትንና እየተቀበሉ ያሉትን የእምነት አባቶች የሚቃወም አይደለም አይሆንምም::

በተደጋጋሚ እንደተገለጠው በሐዋርያት ትምህርት ላይ ተመስርታ በእውነተኛ አባቶች ቅብብሎሽ ወንጌልን ተቀብላ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ትሰብክ የነበረችው ቅድስት ቤተክርስቲያን በየጊዜው እየሾለኩ በገቡባት የክፉዎች ትምህርትና የመናፍቃን ሤራ አማካኝነት ከክርስቶስ ይልቅ ተቆጥሮ የማያልቅ፣ ጠርተንም የማንጨርሰው ሰውና መላእክት፣ እንዲሁም ልዩ ልዩ ፍጥረታት በክርስቶስ አውደ ምህረት ላይ እንድትሰብክ አድርገዋት፡ አዲስ ኪዳን ተቀብያለሁ የምትለዋ ቤተክርስቲያናችን የአዲስ ኪዳን መካከለኛና ዋስ፣ ሊቀ ካህናትም ሆኖ በተወደደ አባቱ በሰውነቱ ከተሾመልን ከክርስቶስ ሌላ እንግዳና በወንጌል ያልተፈቀደ ትምህርትና ሥርዓት እንድትይዝ በማድረጋቸው፣ ይህን ከየት አመጣችው ? ይህም ልማድ ባዕድ፣ የመናፍቃንም ነውና ይወገድ የሚል ነው::

መላእክት ቢሆኑ ወይም ቅዱሳን የምንላቸው ሰዎች፣ (ያውም እንደወንጌል ለጌታ ኖረው ከሆነ ነው) ትምህርታቸውን ተከትለን ፣የኑሮአቸውን ፍሬ ተመልክተን በእምነት እየመሰልናቸው ከመገኘት ውጪ የሞቱበት፣ የተቀበሩት፣ የተፈጩበት፣ ያረጉበት፣ ቃል ኪዳን የተቀበሉበት፣ መታሰቢያቸው የሚደረግበት ቀን ወርና ዓመት ምህረት እያልን እነሱን እንሰብካቸው ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም::

በቅዱሳን ሰዎችና መላእክት ስም የክርስቶስን ለፍጡራኑ በመስጠት፡ አውደ ምህረቶቻችን ጠዋት እና ማታ በእነዚህ ሰዎች ስብከት ተሞልቷል:: ቅዱሳን የምንላቸው በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ያስተማሩን፦ ሰዎች ሊሰግዱላቸውና ሊያመልኳቸው ባሰቡ ጊዜ እንደናንተ እግዚአብሔርን የምናመልክ ሰዎች ነንና ተዉ፡ በማለት እንደከለከሉ ነው:: (የሐ ሥራ 14፣11 - 15)

ቅዱሳን መላእክትም ለሰዎች በተገለጡ ጊዜ ሊሰግዱላቸው ሲያስቡ ክርስቶስን የሚያገለግሉ ባሪያዎች እንደሆኑና ለእግዚአብሔር ብቻ እንዲሰግዱ ከማስጠንቀቂያ ጋር ከልክለዋል:: ራእይ 19:10

ሐዋርያው ጳውሎስም በቆርንቶስ ቤተክርስቲያን ለነበሩ ሰዎች ሲገልጽ እኔ የአጵሎስ፣ እኔ የኬፋ፣ እኔ የክርስቶስ ነኝ እያሉ በእጣ እየተባደኑ እንደዛሬው እንደኛዎቹ ሰባክያነ ፍጡራን፡ በስማቸው ጽላት ለማስቀረጽ ጥቂት

ለቀራቸው ሲናገር፡- አጵሎስ ምንድን ነው? ጳውሎስስ ምንድን ነው? በእነርሱ ያመናችሁ አገልጋዮች ናቸው። ለእያንዳንዳቸው ጌታ እንደሰጣቸው ያገለግላሉ።

እኔ ተከልሁ አጵሎስ አጠጣ ነገር ግን እግዚአብሔር ያሳድግ ነበር እንግዲያስ የሚያሳድግ እግዚአብሔር እንጂ የሚተክል ቢሆን የሚያጠጣ ቢሆን አንዳች አይደሉም፡ ነገር ግን እያንዳንዱ እንደ ራሱ ድካም መጠን የራሱን ደመወዝ ይቀበላል በማለት ገልጧል። ( 1ቆሮ1:10 - 13 1ቆሮ3:5 - 9 )

በሌሎች ድካም ሳይሆን በክርስቶስ ወደ እግዚአብሔር አብ እንድንገባ በር ተከፍቶልን እያለ (ኤፌ2:17 )፣ራሳችንም ሙሉ ደሞዝ ለመቀበል መትጋት ሲገባን (2ዮሐ1:8)ሕዝባችን በሌሎች ድካም መንግሥተ እግዚአብሔር ይገባል በማለት ይህን የመናፍቃኑ ስብከት ምዕመኑን ከክርስቶስ አርቆታል። ስለሆነም ይህ በከፉዎች ወደ ቤተክርስቲያን የገባው ስህተት ይታረም መናፍቃንም ይውጡ ተባለ እንጂ ከፉዎች እንዳሉት ቤተክርስቲያን ትፍረስ ሃይማኖት ይፋለስ አልተባለም።

የሚወደን እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያናችን መታደስ፥ ለሀገራችንም መፈወስ ፥ ባለፉት 500 ዓመታት ውስጥ ለንስሐ የሚያበቃ መልእክት በባሪያዎቹ በኩል ልኮ እንደነበር ታሪክና የታሪክ ድርሳናት ያረጋግጡልናል። እንደሚታወቀው ሁሉ በልዩ ልዩ ምክንያት ወደ ቤተክርስቲያናችን የገቡና እንዲገቡም ፈርቀዳጅ በመሆን ያስተናገድናቸው ጸረ ወንጌል፥ጸረ ክርስትና የሆኑ ትምህርቶችን፣መጻሕፍትን እንዲሁም ሥርዓቶችና ባህሎች (ልማዶች) ወጥተው ቤተክርስቲያን በተመሰረተችበትና በተተከለችበት በእግዚአብሔር ቃል ታድሳ፡ ከገባችበትም ውድቀት፡ ወጥታ ወደ ቀደመ የወንጌል ክብር እንድትመለስ ወንጌልን መሠረት፣ ትምህርተ ሐዋርያትን አብነት፣ ሐዋርያትን የተከ ቅን መምህራንን ቀለም አጣቅሰው ይህ ስህተታችን ነው ይህ በዚህ ይታረም በማለት ተነስተው ነበር።

እነዚያ በወቅቱ ይህን ጥያቄ ይዘው የተነሱት የእግዚአብሔር ሰዎች ከነገሥታት እስከ ጭፍራው ከታላላቅ የሃይማኖት መሪዎች እስከ ተራው ምዕመን ድረስ ተለምዶና በመንግሥት ሥልጣን በካህናቱም ግዝት በአዋጅ ይደረግ የነበረው ለምስል፣ ለቅርጻ ቅርጽ ፣ ለነገሥታት፣ ለሕንጻ ቤተ መቅደስ ፣ በየቦታው ተተክለው ለሚገኙ መስቀለኛ እንጨቶች ስግደት ፣ በቅዱሳንና በመላእክት ስያሜ ለተሳሉ ስእሎች እንዲሁም በሞቱ ሰዎች ስምና ወደ ሞቱ

ሰዎች ጸሎት ማድረስ ወ.ዘ.ተ የእውነተኛይቱ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ትምህርት አይደለም። ሐዋርያትም ይህን ትምህርት እንዳላስተማሩ በመመስከር ሕዝቡም ከእነዚህ ስህተት ትምህርቶች እንዲወጣና ራሳቸውም ትምህርቶቹን በመቃወም ተነስተው በቤተክርስቲያንም እርምት እንዲደረግ አቅርበው እንደነበር ታሪካቸውን የያዙ መጻሕፍት ይመሰክራሉ። ( መጽሐፈ አኃው ተአምረ ማርያም)

ስህተቱ እንዲታረም ወደ ቀደመው የሐዋርያት ትምህርት እንመለስ ብለው የተነሱት ሰዎች መሪ የነበረው መነኩሴ አባ እስጢፋኖስ « ለማርያምና ለመስቀል (ለእንጨቱ) የሥላሴ ክብር ይገባቸዋል በክብር ከሥላሴ ጋር ተካክለዋልና » ስግደት ይገባቸዋል የሚለውን ወንጀል ሲቃወም « አንሰ ኢይሰግድ ለባዕድ ዘእንበለ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ » ትርጉም « እኔስ ለአብ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ እንጂ ለባዕድ አልሰግድም » ብሎ እንደነበር መዘክሮቹ ያስረዳሉ።

ይህን ጥያቄ በአግባቡ አስተናግደን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መፍትሄ ከመስጠት ይልቅ ለስእልና ለምስል ጥብቅና የቆምን እኛና የእኛዎቹ ግን ከሳሽ ምሥክርና ዳኛ ሆነን «ከፍ ብሎ ከአንገት ዝቅ ብሎ ከባት » በሚለው መዝሙራችን ፃኅላስና ቋንጃቸውን በመቁረጥ አፍንጫቸውን በመፎነን ነፍሳቸው የተረፈውንም ደግሞ በሕይወተ ሥጋ እንዳሉ ከአንገታቸው በታች በጉድጓድ በመቅበር የቀንድና የጋማ ከብቶች በራስ ቅላቸው ላይ እንዲነዳባቸው አድርገናል።

ይህን ታሪካችንን ተአምረ ማርያም የተባለው መጽሐፍ በዚህ ግብራችን እግዚአብሔር ተባብሮ ለረጅም ቀን የሚቆይ ብርሃንን በከተማዋ ላይ በመትከሉ የከተማዋ ሥም ደብረ ብርሃን እንደተባለ በመተረክ የነፍሰ ገዳይነታችንን በዓል የእመቤታችን ተአምር ተብሎ እስከ ዛሬ የምናከብረው ሆኗል።

ጥያቄ አቅራቢዎቹ ይዘውት የተነሱት መጽሐፍ ቅዱሳዊ የነበረ ለመሆኑ ራሱ ተአምረ ማርያም እንዲህ ሲል ገልጦታል። « ለመስቀልና ለማርያም አንሰግድም አሉ » ( ተአምር ) ቅን ልብ ያለውና እውነተኛ ክርስቲያን ለማርያም ሆነ ለተቀረጸው እንጨት ስግደት ያስተማረ ሐዋርያ ወይም ደቀመዝሙር ይኖራል ብሎ አያስብም ።

የማይቻለውን የእግዚአብሔር ክንድ እየታገልን የማይጠፋውን እሳት ልናጠፋ በእጃችን የነበረውን ሥልጣነ መንግሥትና ሥልጣነ ክህነት ተሸፍነን በርካታ ለቤተክርስቲያናችን ፈውስ የተላኩትን ቅዱሳን ያለ ርኅራኄ ገድለናል አስገድለናል::

የአይሁድ ካህናት ምክንያት በማፈላለግ፣ ሕዝቡን ለአመጽ በማነሳሳት ነገሥታቱ ደግሞ ክርስቶስን ለመስቀል እንደተባበሩ እኛም ግብረ አይሁድን አሳምረን ደገምነው::« የሚገድሏችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ የሚመስልበት ዘመን ይመጣል ያለው ይሆንን ?» (ዮሐ16፣2 ) የሚያሳዝነው በዚህ ዘመን ላይ ያለነው እንኳ ከዚህ ስህተታችን ለመማር አለመታደላችን አልያም አለመፈለጋችን ነው::

<u>በቅርቡ አስቀድሞ እግዚአብሔር ጀምሮት የነበረውን የወንጌል እሳት እንቅስቃሴ መቅደስ እንዲገቡ በማንፈቅድላቸው፣ ሕጻናት እያልን በናቅናቸው፣ ብላቴኖች አፍ የወንጌሉን ቃል ያለ አስተማሪ በአፋቸው አኑሮ እኛና የምንመራት ቤተክርስቲያን ከውድቀቷ እንድትመለስና ከእግዚአብሔር ጋር ያላትን ግንኙነት እንድታድስ ሲናገረን « የአብርሃም ልጆች ነን እያሉ የአብርሃምን ሥራ እንደማይሰሩት አይሁድ ክርስቶስን እናገለግላለን የምንል እኛ የክርስቶስ የሆኑትን ማሳደድ ማባረር ተያያዝነው::</u>

ወንጌል ሰብኮ የሳተን መመለስ ከወንጌል የወጣን በወንጌል ቃል አውግዞ መለየት ሃይማኖታዊ መመሪያ እያለን መጽሐፍ ዘርግቶ ቃለ እግዚአብሔር ጠቅሶ መርታት ማስረዳት አልሆን ቢለን <u>« የጠጣን ልጅ በዛፍ የመናፍቅን ልጅ በመጻፍ የሚችለው የለም » በሚለው የካሮች መመሪያ ለመጽሐፍ ጊዜ ሳንሰጥ ሰይፍና ቆመጥ ድንጋይና ካራ በመባረክ ምዕመናንን በማሰለፍ ለብዙ የቤተክርስቲያናችን ወጣቶች ሞት፣ አካል መጉደል፣ሀብትና ንብረት መውደም አይነተኛ ሚና ተጫውተናል:: ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ መርታት ያቃተንን ሁሉ መናፍቅ ለማለታችን መረጃ ሆኗል::</u>

ለእግዚአብሔር መልእክት እምቢ ያልን እኛ እያደሩ በክፋት መሰልጠን እያደሩ በበደል መወፈር እንደ ዕድገት ቆጥረነው ወንጌል ይዘው የተነሱትን ወጣቶችና (ወንዶችና ሴቶች ልጆች) የወንጌሉን ባለቤት ጌታችንን ሳይቀር እየተቃወምን እንገኛለን::

መቅደሱን በከለከልናቸው ሕጻናት እግዚአብሔር ገሰጸን « አንተም እውቀትን ጠልተሃልና እኔ ካህን እንዳትሆነኝ እጠላሃለሁ » ( ሆሴ 4:6 ) የተባለው ደርሶ ይሆን ? እነዚያ ወጣቶች እንደ እኛ ልብሰ ተክህኖ ሳይለብሱ፣ እንደኛ ጥምጥም ሳይጠመጥሙ፣ መስቀል በእጃቸው ሳይጨብጡ ፣ ያለ ጠበል (ውሃ) እንደኛ ሳይደቁትና ሳይቀስሱ ሳይመነኩሱ ከአፋቸው በሚወጣ ቃለ እግዚአብሔር የብዙዎች መንፈሳዊ ዓይን በራ ፣ አጋንንት ተባረሩ ድውዮች ተፈወሱ ። « እኔ ቆሜ የእግዚአብሔር መንፈስ በየት በኩል ወደ አንተ አለፈ »( 2ኛዜና 18:23) በሚለው ትዕቢታችን እንደ ግብር አባቶቻችን አይሁድ ማሳደድ ማውገዝና ማስወገዝ ተያያዝነው። ቢጨንቀንም « ቁሳርን ይቃወማል » እንዳሉት ጌታን ውርደታችንን እንዲያግዙን ወጣቶቹ የፖለቲካ ድርጅቶች ናቸው መንግሥት ተቃዋሚዎች ናቸው አልን ለጥቂት ጊዜም ቢሆን አሳሰርን ። እውነቱ ሲገለጥ ግን መና ሆነ።

የፈራነውና የተቃወምነው የእግዚአብሔር ክንድ ግን ከወጣቶቹ አልፎ መቅደሳችንን እንኳኒ ዲያቆናት በወንጌሉ ተያዙ ቀሳውስቱ ተነኩ መነኮሳቱ ተሸነፉ አንቱ የተባሉት ሽማግሌ ተረቱ ሰው በማይደርስበት ገዳም የልዑል እጅ ገባች የማይጠፋ እሳት ነደደ ። « እሳት ልጥል መጣሁ ከነደደች ምን አደርጋለሁ » እንዳለ ጌታ። ( ሉቃ 12: 39 )

በዚህ ሁሉ ያልተማርነው እኛ አጋንንት ይዟቸዋል የሚመራቸው ሰይጣን ነው አልን « በብኤል ዜቡል አጋንንትን ያወጣል» እንዳሉት ጌታን » ( ማቴ12:24 ) በሞት የሚገደብ የወንጌል እሳት ፣ በስደት የሚቆም የእግዚአብሔር ክንድ የለምና እኛ ባንማርም ባይገባንም ሰውን የሚወድ እግዚአብሔር እሳቱን በሁሉም የሃገሪቱ ክፍሎች ለኮሰው የማንጥለውን እየታገልን ዘመናችን አለቀ።

እንደ ውግዘታችን እንደ ማሳደዳችን ችግሩ በተወገደ ነበር ግን ባሰ እንጂ አልቆመም፡ የወጣቶችን ጥያቄ ለምን እንዲህ ፈራነው ? ለምንስ ገሃድ ወጥቶ ሕዝብ አያውቀውም ? በደፈናው ጸረ ማርያም ጸረ ቤተክርስቲያን እያልን መጮሁ አሁን አያዋጣንም። በእያንዳንዳችን ቤት ነገሩ ገብቷልና ። የምንታገለው ልጆቹን ሳይሆን እግዚአብሔርን ነውና ቆም ብለን ብናስብ ራሳችንንም ቤተክርስቲያናችንንም ከውድቀት እናድናለን።

የሊቃውንት ጉባኤ ፣ የካህናት ጉባኤ ፣ የሰበካ ጉባኤ፣ የሃገር ሽማግሌዎች ጉባኤ (ኦርቶዶክሳውያን) መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርገን ለችግራችን መሠረታዊ መፍትሄ ካልወሰድን የፈራነው ገፍቶን እግዚአብሔርም ንቆን ከመውደቅ አንድንም:: እረ ለመሆኑ በማሳደዱ እንቀጥል? ወይስ የእርምት እርምጃ መውሰዱ ይሻላል? እውነቱን እውነት ሐሰትን ሐሰት ማለት ማንን ጎዳ ? ልናስቀመው የማንችለውን የእግዚአብሔር ክንድ በዕድሜ በምትገደብ ሰውነት መቋቋም ይቻላልን ?

<u>ባለፉት 12 ዓመታት ብቻ ስንቶችን በራሳችን እጅ ያጠመቅናቸውን ፈጀን ለስንቱ ሞት፣አካል መጉደል፣ ለስንቱስ ሀብትና ንብረት መውደም፣ ለስንቱስ ትዳርና ሥራ ፍቺ ምክንያት ሆነናል ? በመቀሌ፣ በድሬዳዋ፣ በሐረር፣ በአዲስ አበባ፣ በጅጅጋ፣ በደብረ ማርቆስ፣ በባህር ዳር፣ በደብረ ብርሃን፣ በጎንደር፣ በባሌ፣ በጅማ ወ.ዘ.ተ ስንት መከራ ተፈጠረ</u> ?

ብዙ ሰዎች በበተክርስቲያናችን ስለተፈጠረውና መቋጫ ስላጣው የወጣቱና የጥቂት አገልጋዮች ግጭት ምክንያት ስለሆኑት የስሕተት ትምህርቶችና መጻሕፍት አንስተው ሲናገሩ « እነዚህ ዕድሜአቸው 40 ዓመት እንኳ በቅጡ ያልሞላ ውርጋጦች ዛሬ ተነስተው ቤተክርስቲያኒቱ ተሳስታለች በውስጧም ስሕተት ገብቷል መጻሕፍቶቿም ይታረሙ ሲሉ አያፍሩምን .... ? ምድረ ቂጫጭ ዛሬ ተወልዶ ...... ያልጠረገ ሁሉ መጻሕፍቶቻችን ይህን ያህል ዘመን (2000 ዓመት ማለታቸው ነው ) ሲኖሩ የቀደሙት አባቶች ስሕተት ናቸው ያላሏቸውን ...ምናምናቴ ሁሉ ተሰባስበው አፋቸውን ሞልተው ስሕተት ናቸው ይላሉ: .... ስሕተት ቢሆኑ ኖሮ እግዚአብሔር ያጠፋቸው አልነበረምን ? » በማለት በቁጭት ሲናገሩ ይሰማሉ::

በእርግጥ እንዳሉት በመጻሕፍቱ ውስጥ ስሕተት ብቻ ሳይሆን ክህደትና ወንጀል አለ:: ቢያስፈልግ በመጽሐፍ ቅዱስ እየተመዘኑ ይታዩ በማለት የተነሣው ትውልድና ወንጀል ተሸክመዋል ለፍርድ ይቅረቡ የሚባሉት መጻሕፍት የዕድሜ ልዩነት የሰማይና የምድር ያሕል ነው:: ተናጋሪዎችም ሆኑ የመቅደሱ ሠራተኞች የሳቱት እዚህ ላይ ነው:: በሃገራችን እንኳንስ የሃይማኖት መጽሐፍ ነው ተብሎ ይቅርና ዕድሜ ጠገብ ዛፍ እንኳ ይከበራል ይመለካልም:: ይህም ልማዳችን ለዛሬው ስሕተታችን ዳርጎናል:: አይሁድ በ30 ዓመቱ ወንጌለ መንግሥትን ይሰብክ የነበረውን ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስን እንዳይቀበሉት ያደረጋቸው አንዱ እነሱ( አይሁድ) እንዳሉት የዕድሜው ማነስ ነበር « 50

ዓመት ያልሞላህ አንተ...» ይሉት ነበርና፡፡ እነሱ የሚያውቁት እንደነቀያፋ የጠመጠመ ፣ አሸንክታብ በደረቱ በትክሻው ያንጠለጠለ፣ ጢሙ መሬት የነካ ፣ መሆን ነበረበት ፡ ጌታችን ግን በ30 ዘመኑ እንደባለሥልጣን ቃል ይናገር ነበር ተብሎ ተጽፎለታል፡፡

እኛም ኢትዮጵያውያን ይህ ያጠቃናል፡ ለሽምግልና የምንሰጠው ክብር ገደቡን ባይለቅ እውነትንም ባይሸፍንብን ባህልነቱ መልካም በሆነ ነበር፡፡ ዕድሜው ለረዘመ ሁሉ ለምንሰጠው ከገደብ ያለፈ ትርጉም የተተረተ ነገር አለ « ... እኅትና ወንድም የሆኑ ወጣቶች በመንገድ ሲሄዱ ከዕድሜው ረዝማኔ የተነሳ ቆዳው የተጨማተረ ጠጉሩ የተላላጠ ደካማ ውሻ አገኙ ወንዱ ልጅ ድንጋይ አንስቶ ያን ያረጀ ውሻ ሲመታው ሴቷ ልጅ እጅግ ተሸማቃ « ምን ማለትህ ነው ? አባትህ አይሆንም ? » አለችው ይባላል፡፡ ምንም እንኳ ውሻውን የመምታቱ ምክንያት ባይገለጥም እንስሳውን እንዲመታው ባንደግፈውም በምንም ምክንያት ለልጁ አባት እንደማይሆን ግን ደፍረን እንናገራለን፡፡

ይህ የሚያሳየን ዕድሜ ጠገብ የሆነ ማናቸውም ነገር እኛን መግዛት እንደቻለ ነው፡፡ ሽበት ሁሉ የመልካም ሽምግልና ምልክት አይደለምና እውነትን በእድሜ ልንመዝነው አይገባም፡ የእድሜ ርዝመት እውነት ለመሆን እንደመረጃ የምንጠቀም ከሆነ በፍጥረት ታሪክ « ሰይጣን» ያስቆጠረው ዕድሜ ራሱን እውነተኛ እንዲያደርግ እያገዘነው እንዳይሆን መጠንቀቁ ያሻል፡፡ ለሰይጣን የዕድሜው ብዛት እውነተኛ ለመሆን እንዳልረዳው ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም በሥጋ ተገልጦ በምድር በተመላለሰበት ጊዜ ስለሰይጣን ሲናገር « ..እርሱ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነው » በማለት ለዕድሜው ሳይሆን ለውስጣዊ ማንነቱ ትኩረት ሰጥቶ ተናገረ፡፡

በመሆኑም ዕድሜ ጠገቦቹ መጻሕፍትና የይታረሙ ጥያቄ አቅራቢው ትውልድ መመዘን ያለባቸው በተሰፈሩበት ዕድሜ ሳይሆን በተሸከሙት ውስጣዊ ማንነት ላይ ነው ፡፡ ቤተክርስቲያንም ለመጻሕፍቶቿ ክብር መስጠት የሚገባት ዕድሜአቸው ሰማይ ስለነካ ሳይሆን ሲገለጡ በሚናገሩት ቁም ነገርና እውነት መሆን ይገባዋል፡፡ ዛሬ በቤተክርስቲያናችን አንቱ የሚያሰኝ ማዕረግን የሚያስጡ ዕድሜ ያላቸው መጻሕፍቶቿ ጉዳይ በዕድሜአቸው ርዝማኔ ከተሰቀሉበት እንዳናወርዳቸው ሽምግልናቸውእያስፈራራን በውስጣቸው መርገምን ተሸክመው እኛ ግን ቅዱስ ቅዱስ እያልን ተሸክመናቸዋል፡፡

በሀገራችን 25ኛው ሱራፌል /የሰማይ ካህን/ በተባሉት በአባ ተክለሃይማኖት ስም በተጻፈው መጽሐፍ ውስጥ እንዲህ የሚል ዕድሜ ጠገብ ወንጀል ተቀምጧል፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ተክለ ሃይማኖት መጥቶ እንዲህ አለው « ... በተቅማጥ በሽታ ትሞታለህ እርሷንም ( ተቅማጥህን ማለቱ ነው ) እንደስቅለቴና ከአንተ በፊት እንደነበሩ ሰማዕታት ደም አቆጥርልሃለሁ » ይላል። የሚገርመው ከዛን ጊዜ ጀምሮ በዚህ ገዳም በተቅማጥ በሽታ የሚሞቱ ሁሉ ያለምንም ችግር መንግሥተ ሰማያት እንደሚገቡ የሚናገረው ክፍል ነው።

እንደ ገድሉ ትረካ መጽሐፉ በ1399 ዓ.ም በአጼ ይስሐቅ ዘመነ መንግሥት ዕጨጌ ዮሐንስ ከማ በተባለ ሰው እንደተጣፈ ይናገራል። ልብ እንበል የተክለ ሃይማኖትን ተቅማጥ የኃጢአተኞችን ዕዳ ለመክፈል ከፈሰሰው ከክርስቶስ ደም ጋር አስተካክሎ « ተቅማጥህ እንደ ስቅለቴ ደም ነው » ማለቱ ምን ያህል ርግማን ተሸክመን እንደኖርን በቂ ማስረጃ ነው።

የሕያው እግዚአብሔር ቃል የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ግን » ... የኪዳኑን ደም እንደ ርኩስ ነገር የቆጠረ ... እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል ...» በማለት ከዚህ ቅጣት እንድንተርፍ ይመክረናል።

ገድሉ « ... እሁድና ማክሰኞ አባብ የገደለ ኃጢአቱ ይሰረይለታል ...» ይላል / ገድለ ተክለሃይማኖት ም»51 ፡ 6 / መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የኃጢአት ሥርየት አለ ይላል፡ /1ዮሐ1፡7፣ 1ጴጥ1፡18፣ ዕብ9፡14/

ታዲያ ዕድሜ ይህን የመሰለ ክሕደት እውነት እንዲሆንለት ይረዳዋልን ? በጭራሽ አይሆንም። መጻሕፍቱን / ዕድሜ ጠገቡን ማለታችን ነው / ማንበብ አታስታጉሉ ያስታጎለ መጻሕፍቱን የተጠራጠረ እንደሚቀሰፍ በረከት እንደሚነጠቅ እያስፈራሩ እስካሁን ተሰውረው ቢቆዩም ከዚህ በኋላ ግን መሸገሪያ የላቸውም ቅጣት ከሰማይ መጥቶባቸዋልና።

በግዝት የማስፈራሪያ ቃላት ቢከፈሉና ይህም ረድኤታቸው ዕድሜአቸው ቢቆለልም እንደተባለው 40 ዓመትን ባልደፈነ ግን በልዑል ጸጋ በታመኑ ልጆች መፍረሳቸው አይቀሬ ነው። ዕደሚው የረዘመ ሁሉ እውነት አይደለምና፡

በቤተክርስቲያናችን ስለተከሰተው መንፈሳዊ ችግር መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት፣ እውነተኛ ሊቃውንትን ምሥክር፣ ትምህርተ ሐዋርያትን አብነት በማድረግ ውሸቱን ውሸት እው ነቱን እውነት ነው በማለት ቤተ ክርስቲያን

እራሷን እንድታ ስተካክል መፍትሄ መፈለግን እንደውርደት እየቆጠርን ቤተክር ስቲያናችን የክርስቶስን ያህል ፍፁም፣ እንከን የሌለባት፣ ንጽሕት፣ ቅድስት ናት በሚለው ጀብደኝነታችን ተጀቡነን እነሆ ከውድቀት ወደ ውድቀት፣ ከክስረት ወደ ክስረት እየጣልናት እንገኛለን ::

ስማችን ሳይሆን ግብራችን በሚታይበት ዘመን ላይ ቆመን ግብራችንን በስማችን ለመሸፈን እየታገልን የንስሐ ጊዜያችንን በከንቱ እናባክናለን:: የአይሁድ ችግር የእኛ ባሕርይ ሆኖ ጽድቅ ቅድስና ከእኛ ወዲያ ላሳር በሚለው ዜማ አጃቢ እያበዛን ራሳችንና ተከታዮቻችንን ለፍርድ እያዘጋጀን እንገኛለን ::

ሰው መሆናችንን ዘንግተን፣ አባቶቻችን ያልናቸውም እንኳ ሰው እንደሆኑ ማመን ተስኖን « አበው ደንግገዋል ሠለስቱ ምዕት አውግዘዋል » በሚል ሽፋን ወንጀላችንን ከመናዘዝና ይቅርታ ከመጠየቅ ይልቅ የወንጀላችን ጀማሪዎችና አጽዳቂዎች አበው ሐዋር ያት፣ ሠለስቱ ምዕት ነበሩ ናቸው የእነርሱንም ቃል አንሽርም ብለን እንበለ ንስሐ እንኖራለን ::

እውነተኞች የእግዚአብሔር ሰዎች ሁልጊዜ ጸሎታቸው « በእውነተኛ ሚዛን ልመዘን ... በሐሰት ሄጄ እንደሆነ እግሬ ለሽንገላ ቸኩሎ እንደሆነ እርምጃዬ ከመንገድ ፈቀቅ ብሎ እንደሆነ ..... ነውርም ከእጄጋር ተጣብቆ እንደሆነ .... / (ኢዮ 31 :5-7) ይላሉ::

እንደ እግዚአብሔር ልብ ተብሎ የተጠራው ዳዊት «ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን ነው (መዝ 118:105) በማለት ሁልጊዜ አረማመዱን (መንፈሳዊ ጉዞውን) የሚመዝንበትና የሚያይበት ሕጉ (ቃሉ) እንደሆነ ዘምሮአል ::

ቤተክርስቲያን ( የምእመናን አንድነት ) ስሕተት አግኝቷት ወንጀል ገብቶባት አያውቅም የሚል የዋህነት ይዞን ቤተክርስቲያናችን መንፈሳዊ ተልዕኮዋን (አረማመዷን) በቃሉ ብርሃንነት ቆም ብላ እንዳታይ ገብዘናታልን ::

በክርስቶስ ስም የተተከሉትን ሰባቱን አብያተክርስቲያናት ለተ መለከታቸው ይህን ግብዝነታችንን ሊያፈርሱልን ይችላሉ :: ራሳቸው ሐዋርያት በአካለ ሥጋ እያሉ የተከሏቸው የቆሮንቶስ ፣ የኤፌሶን ፣ የገላትያ ፣ የተሰ ሎንቄ ፣ ወ.ዘ.ተ አብያተክርስ ቲያናት በውስጣቸው የስህተት ትምህርት ፣ ለጆሮ የሚሰቀጥጥ ኃጢአት ገብቶባቸው እንደነበረና ሐዋርያትም የእምነት እርምጃ

እየወሰዱ የቤተክርስቲያንን ተልዕኮ ማስተካከላቸውን መልእ ክተ ሐዋርያትን ማየቱ በቂ ነው

በቤተክርስቲያን መረብ መልካሞች ብቻ ሳይሆኑ ክፉዎችም እየገቡ (ማቴ 13: 47-49) በንጹሕ ስንዴ መካከል እንክ ርዳዶች እየበቀሉ (ማቴ13:24-30) ለቤተክርስቲያን ችግር እንደ ሚሆኑ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስተምሯል ።

ሐዋርያት ቤተክርስቲያንን ለተተኪ አገልጋዮች ሲሰጡ « ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ጠማማ ትምህርትን እያስተማሩ የምዕምናን ልብ የሚጎትቱ መናፍቃን በቤተክርስቲያን ሊነሱ እንደሚችሉ በክታባቸው አሳስበዋል (የሐዋ 20 - 30)

ይህም ቤተክርስቲያን በየጊ ዜው እርምጃዋን ፣ አገልግሎቷን ፣ ተልዕኮዋን ፣ አገልጋዮቿን ምዕመናቿን እየመረመረች - ሐሳበ ሰይጣንን « ሑር እምድኅሬየ ሰይጣን » ሐሳበ ሠናዩን « ብፁዕ አንተ » በማለት ( ማቴ 16 - 16 : 23 ) እየለየች በእጇ ነውር ቢገኝ አምዘግዝጋ በመጣል በእጇ ያለውን እውነት ከፍ አድርጋ በመመስከር እንድትነቃ የሚያስገ ነዝባት ነው

ያ ባይሆን ከውጪ ብቻ ሳይሆን ከመንጋው መካከል የተቀመጡ ክፉዎች ተልዕኮዋን ሆነ የምዕመኗን ልብ በመጎተት መንገዷን በድጥና በክረምት ያደርጉባታል:: እድሜያችን ብቻ ውን ለንፅሕናችን ምሥክር አይሆንም:: እንኳንስ እድሜ ሕግ፣የመቅደስ ሥርዓት፣ አባ ቶች፣ ክርስቶስ እንኳ በሥጋ ከእነሱ የሆነላቸው አይሁድ እንደተጣሉ እናውቃለንና::(ሮሜ 9:1- 5ሮሜ10: 1-4

ስለሆነም ቤተክርስቲያንን ይጠብቋት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ጳጳሳት አድርጎ የሾማቸው አባቶች ለመንጋውና ለራሳቸው ጭምር ተጠንቅቀው እንዲኖሩ ማለትም በየጊዜው የቤተክ ርስቲያንን ተልዕኮ እየመረመሩ፣ እየጎበኙ የሐሰት ትምህርቶችንና ሥርዓቶችን በእንጭ ጭነታቸው እንዲያስቀሯቸው የቀናውንም ትምህርትና ሥርዓት ለማምጣት ከፍተኛ አደራ ተጥሎባቸዋል ::

አንዳንዶች ወገኖቻችን (በቤተክርስቲያን አብረውን ያሉ) ስማችንን እንደ ሰንደቅ ከፍ አድርገው የቀናን ፣ የነፃን ፣ እንከን የለሽ ፣ ንፁህና ፊፅም ስህተት የማይነካን ነን እያሉ በቤተክርስቲያን ገብቶ ዙፋኑን የዘረጋውን የሐሰት ትምህርት ለዕድሜ ማራዘሚያ መድኃኒት በመሆን እየደገፉት ይገኛሉ::

የእድሜ ባለጠጋዋ ቤተክርስ ቲያናችን ደጋግመን እንደገለጥነው በደረሱባት ውጫዊና ውስጣዊ ችግሮች መንሥኤ በተመሠረተችበት ንፁህ ወንጌል እንዳትገኝ በቂ ምክንያት ሆነው መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነው ትምህርቷ መልካም በሆነ ሥር ዓቷ ላይ ስርዋፅ የገቡ የሥ ሕተት ትምህርቶች መገኘ ታቸው ፀሐይ የሞቀው ጉዳያችን ነው ::

ይህን ችግር ለመቀበል እና አለ ብሎ ለማመን ያልተዋጠላቸው መናፍቃን ዓለም ስቶ (ተሳስቶ) እኛ ብቻ እንቀራለን ወደሚለው ምጽድቆሽ እየገቡ የቀናና ቀጥ ያለ ሃይማኖት አለን በሚል ሽፋን ተይዘው ይታያሉ ስም ይዞ መሞት እንደሚቻል ያላወቁ /ራዕ3:15/

ሰዎቻችን ችግር እንዳለ አለማመን ብቻ ሳይሆን ችግር አለብን እናርም የሚሉትንም ለመቀበል ይቸገራሉ:: ይህንንም ችግራቸውን ሕዝብ እንዳያ ውቅባቸው፣ እመቤታችንን የጠሉ ፣ቤተክርስቲያንን የሚያፈርሱ ፣ ሃገር የሚቆርሱ በሚለው መዝሙራቸው ያጅቡታል:: እኛ ከሐዋርያት እንበልጣለን ? ከሐዋርያትስ የተሻለ የክር ስትና ሕይወት ባሕርይ አለንን ? ሐዋርያት እንኳ በጉባኤያቸው በኅብረታቸው ሥሕተት ፣ ኃጢአት ፣ የክህደት ትምህርት ገብቶባቸው እንደነበር አልካዱም

- ገንዘብ የሚሰርቅ /ዮሐ5:1-11/
- ትንሣኤ ከአሁን ቀደም ሆኗል የሚሉ /
- ለደኅንነት መገረዝ ይጠቅማል የሚሉ /ሐዋ15:5/
- የወር በዓል ፣መብል ፣መጠጥ ፣ ለጽድቅ ያስፈልጋል የሚሉ /ቆላ2:16-23/
- የአባቱን ሚስት ያገባ ምእመን /1ኛ ቆሮ4/
- በቤተክርስቲያን ተሹመው ሐዋርያ ትንና የሐዋርያትን ተከታዮቻቸውን የሚቃወሙ ወ.ዘ.ተ እንደነበሩ በግልጥ በመልእክታቸው አስፍረዋል::/ሦስተኛ የዮሐንስ መልእክት በሙሉ/

እንግዲህ የሐዋርያት ቤተክር ስቲያን ምሥረታ ገና እድሜው ከ50 ዓመት ያልበለጠ መሆኑን ስናይና የ1600 ዓመት ዕድሜ ባለጠጋዋን ቤተክርስ ቲያናችንን ስንመለከት የችግ ራችን ስፋትና ግዝፈት ቁልጭ ብሎ ይታየናል::

50 ዓመቱን በቅጡ ያልደፈነ፣ ከጌታ ጋር እየኖሩ በተማሩ በልዩ ጥሪና ሥልጣን ወንጌልን እንዲሰብኩ የተሾሙ ሐዋርያት እያሉ በቤተክርስቲያን እንዲህ ያለ ችግር ነበር ከተባለ: የእኛይቱ ቤተክርስቲያን ያለእንከን ፍጽምት ናት ልንል እንደፍራለን ? ያውም በአደባባይ የተገለጠ ችግር እያለን?::

ታሪክ የሚያስረግጥልን ታላቁ ሰው ሙሴ በእግዚአብሔር ተራራ ወጥቶ ከእግዘአብሔር ጋር ሲነጋገር ሳለ በሰፈር የዋለው አገልጋይ (ካህን) የጥጃን ምስል ሠርቶ ለእስራኤላውያን ከግብፅ ያወጡህ አማልክት እነዚህ ናቸው በማለት ሲያዘምር እና ሲዘምር እንደነበር በእጃችን ያለው መመሪያችን (መጽሐፍ ቅዱስ ) ያረጋግጥልናል ይህም የቤተክርስቲያን አገልግሎት ሁል ጊዜ የአባቶችን /መሪዎችን/ የዕለት ተዕለት ክትትል የሚጠይቅ እንደሆነ የሚጠቁም ነው::

ቤተክርስቲያናችንም ከዚህ የተለየች አይደለችም:: ቅዱሳን አባቶቻችን በፆም በጸሎት በእግዚ አብሔር ፊት ይተጉ የነበሩት በሞት ሲገደቡ በዕድሜ ጣሪያ ሲያዙ አጽራረ ቤተክርስቲያን ትምህርት ማፍለሳቸው፣ ተልዕ እኮ ማሳታቸው ጣታችንን ቀስረን የምናሳየው እውነት ነው :: የሚገርመው ረዥም ዘመን ያስቆጠረው ችግራችን በጊዜውና በወቅቱ እንዳይነቀል ግብራችንን በስማችን ሸፍነን እንከን አልባ ነን እያልን በመከፈላችን የችግራችን ውል መጀመሪያና መፍቻ እስኪጠፋ ማድረጋችን ነው::

ቀላል ያልሆነ ቁጥር ያላቸው ሰዎችም ችግሩን የዛሬ ችግር አድርገው በመውሰድ አስቀ ድመው በፈረንጆች ሲያመካኙ ከቆዩ በኋላ ዛሬ ደግሞ በስም በሚጠቅሷቸው መሪዎቻችን እጅና ሕይወት ላይ በማስቀመጥ ችግራችን ጐጃሜነት፣ ጐንደ ሬነት፣ ሸዋዊነት፣ ትግራዊነት፣ ኦሮሞ አዊነት፣ ጉራጌያዊነት፣ ጋምቤላዊነት፣ ወ.ዘ.ተ ነው በማለት ሕዝቡን እያደናገሩ የችግራችንን ውል በእጅጉ አወሳስበውታል

በእውነቱ ችግራችንን የእነዚህ መሪዎቻችን ጎጃሜነት፣ ጎንደሬነት ትግሬነት ፣ ጋምቤ ላነት ፣ ጉራጌነት፣ መሆናቸው ሳይሆን በማወቅም ይሁን ባለማ ወቀ ከመጽሐፍ ቅዱስ ዓላማና መመሪያ ውጭ እንደወጣን ለማመን አለመታደላችን ነው :: ከዘር ከጎሳ ከቋንቋና ከነገድ በክርስቶስ ደም ከኃጢያት የተዋ ጀውን ያህል ክርስቶስ ዋጅቶናል ( ራይ 5:10) ይህን ባለመረዳት የቤተክ ርስቲያንን ችግር ከዚህ ጋር አዛምዶ ማየት በወንጌል ቃል አለመወለዳችንን ያሳያል ::

ይልቅ እንመንና ለንስሐ እንዘጋጅ በቤተክርስቲያናችን ከረጅም ዓመታት ጀምሮ በመንጋው መካከል የተነሱ መናፍቃን የከተቷቸው የሐሰት ትምህርቶችና ሥርዓቶች እንዳሉ አንካድ ::"የጌታ ቃል እንደሚል እንዴት እንደወደቅህ አስብ ይላል ( ራዕይ 2: 5 ) የተሰጠንን የማስቢያ ጊዜ በክንቱ

አናጥፋ / ራቁታችንን ሆነን የተጎናጸፍን ፣ ደኃ ሆነን ባለጠጋ የሆንን ጌታ ያለን መስሎን በደጅ አስቀምጠን ያለን (ራዕይ 3:15-22 ) እኛ ለእርምት እንነሣ ::ተልዕኮን እየመረመሩ ከብክለት ማጽዳት ሃይማኖትን ማደስ ፣ ቤተክርስቲያንን ማፍረስ አይደለምና

ይህ በልጆችዋ የተፈጠረው ችግር እንዲህ በቀላሉ የሚታለፍ አይደለም ዛሬ የተፈጠረውን አለመግባባት ቤተክርስቲያን የነገር ሁሉ መመዘኛዋ በሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ እየመረመረች መንፈሳዊ መፍትሄ ልትሰጠው ይገባል:: ዕለት ዕለት ቁጥሩ እየጨመረ የመጣው ተሰዳጅ በነገ የቤተክርስቲያኒቱ ዕጣ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከማሳደሩም በላይ የተከበረ ታሪኳንም ሆነ ክርስቲያናዊ ተልዕኮዋን የሚያጎድፍ ሁኔታ ሊያመጣባት ይችላልና አሁን እየተደረገ ያለውን መፍትሄ ያልሆነ መፍትሄ /ማባረርና ማሳደድ / ወደ ጎን በመተው እውነትን ሳንሸሽ ወንጌል ለሚለው ብንሸነፍ ለሀገራችንም ሆነ ለአፍሪቃ ብሎም ለቀረው ዓለም የሚተርፍ በቅዱስ ወንጌል የተነገረልንን ተስፋና ኪዳን አከናውነን እናልፋለን::

በሀገራችን የክርስትና ታሪክ ታትሞ ተሰራጪ ከተባለው ከቅዱሱ መጽሐፍ ( መጽሐፍ ቅዱስ ) 100 ጊዜ እጥፍ እየተዘጋጁና እየታተሙ የሚሰራጩት ፀረ ወንጌል ክታቦች ገድላት ድርሳናት ተአምራት እንዲሁም ለልዩ ልዩ አስማታዊ ሥራ የሚጠቅሙ የጥበብ ወይም የአብነት እያሉ የሚጠሯቸው መጻሕፍት የሕዝባችንን ኅሊና ብቻ ሳይሆን የሀገራችንን ምድር ጭምር ተቆጣጥረውት ይገኛሉ::

በቅዱስ ዕገሌና ዕገሊት ሥም እየተባሉ፤ የሚለቀለቁት መጣጥፎች ወንበሩ አልጠናለት ያለው ንጉሥ ገበያ የቀዘቀዘበት ነጋዴ ትዳሩ የፈረሰበት ጎረምሳ ነፍስ ያጠፋ ወንበዴ ከመርካቶ ያገኘውን ወይባ ልብስ አልያም በርኖስ ቢጤ ይገዛና መነንሁ በቁሜ ሞቻለሁ እያለ ለዓመት ለሁለት ዓመት ከከተማ ዘወር ካለ በኋላ መንፈሳዊ መስሎ መጣላችሁ እመቤቴ ታየችኝ መልአክ ተገለጠልኝ አራት ኪሎ ዘንዶ ይወድቃል እሳት ከሰማይ ይዘንባል ወዮላችሁ ወላጆች ረቡና አርብን የገደፈ ፊቴን አያዩትም ብላለች እመቤታችን ጳጳሱ ጥቁር ይልበስ ጫማውን አውልቆ 3 ወር ንስሐ ይግባ ወዮ ብላለች ድንግል ማርያም እያለ በየቤተ-ክርስቲያኑ ጥግ ፋከራውን ይያያዘዋል::

የሥራ ብዛት ድማቱን ያደከመው ሁሉ ሌሊት የቃዡውን ቅዡት መልአክ ነገረኝ እያለ ወንጌል እንኳንስ ተናግሮት ሲባል ሰምቶት የማያውቀውን የቅዡት ሥዕል ለየዋሁ ሕዝብ እየሰበከ አልቅሱ ደረታችሁን ምቱ ይልና ጣል ጣል አድርጉባት ግሸን ልሄድ ቁልቢ ልገባ እመቤቴ ተናግራኝ እያለ በንግድ ያላገኘ ውን ገበያ በእምነት ሽፋን ያለ ቀረጥ ያለ ታክስ ይነግዳል።

ለእንዲህ ዓይነቱ የመናፍቃን ትምህርት የተጋለጠችው ቤተክርስቲያናችን ሃይ ለማለት ጉልበት አጥታ በባሕታዊና መነኮስሁ ባይ ሁሉ እየተነዳች በትላንቱ ችግሯ ላይ ሌላ ችግርን እያስተናገደች እምነት አልባ በሆኑት ሕዝቦችና ሀገራት እንኳ መሳቂያና መሳለቂያ እየሆነች መጥታለች።

ነገሥታት ለጥቅማቸው ሲሉ የሚፈልጓት ቤተክርስቲያናችን የነገሥታትን ወደ እርሷ መግባት መወደድ እየመሰላት ቁስም ንጉሥም እያደረገች በክርስቶስ ደም ባልተቀደሰ አዕምሮ እንዳሻቸው ሲያደርጓት በምትኩ መልክአ ንጉሥ ዕገሌ እያስደረሰች መወድስና ቅኔ ለነገሥታቱ እያቀረበች የጠራትና የተከላትን ክርስቶስን በመተው ንጉሥ ዕገሌ ይሙትን» ተከታዮቿ ሲለማመዱት መምህራኖቿም ሆኑ ሊቃውንቶቿ «የክርስቶስ ባርያ» ከማለት ይልቅ « ዘራፍ የዕገሌ አሽከር » ይሉ እንደነበር የእኛም ዕድሜ እንኳ ያገኘው ታሪክ ነው።

በተለይ ዘርዓ ያዕቆብ የተባለው ንጉሥና መነኩሴ ነኝ ባይ ፍቅረ ሥዕልና ምስል የተጠናወተው ስለነበር በየቀኑ የሚጸለይ የሚነበብ የሚደገም የሚባሉላቸው መጻሕፍት እንዳሻን እንዲፈሉ ላቅ ያለ አስተዋጽኦ በማድርጉ የመጻሕፍት ሁሉ መመዘኛ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ አጠገቡ የማያስደርሳቸው ተራፊሞች ሁሉ ሥልጣንና ጊዜ አግኝተው ከሰኞ እስከ ሰኞ ከዓመት እስከ ዓመት የምንነበብ የምንደገም እኛ ነን ብለው ቅዱሱንና የእግዚአብሔርን እውነተኛ ቃል በመጋፋት በልጅ በአዋቂው በማይሙ በምሁሩ ኪስ ደረት ቦርሳና መደርደሪያ ተኮፍሰው ይገኛሉ።

እኒህ ባለቤቶቻቸው አዋልድ ያሏቸው ዲቃላ መጻሕፍት ለሃይማኖት ምሥክርነት ለክርክር መፍቻነት የማይጠቀሱ ግና የሕዝቡን ኅሊና ገዝተው የያዙ ዕዳዎች ናቸው። የመጻሕፍቱ ዕድሜ እንዲረዝም ተቀባይነትም እንዲኖራቸው ያደረጓቸው ዓበይት ምክንያቶች መጻሕፍቱ በግዕዝ ቋንቋ መጻፋቸው፣ ሕዝቡ ለግዕዝ ቋንቋ ባዕድና ሩቅ መሆኑና ጸሐፊዎቻቸው

ቤተመቅደስ ውስው ቤተመቅደስ ስለሚኖሩ ከቤተ መቅደስ ክፉ ነገር ይገኛል ብሎ ሕዝቡ ስለማያስብ ሲሆን ሌላውና እስከ አሁን ሕዝቡ ያልነቃበት ምክንያት ግን በመጻሕፍቱ አጋፋሪዎች በተደገመ ሰይጣናዊ ሥራ ማስተዋሉ ስለተወሰደበት ነው።

በቅርቡ በሞት የተወሰዱት የቤተክርስቲያኒቱ ሊቅና ምሁር ናቸው ተብለው የሚታወቁትና በቀብራቸውም ላይ የቤተክርስቲያን አባቶች የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን እጇን ተቆረጠች፣ አንድ ዓይኗን አጣች ሲሉ የመሰከሩላቸው ሰው 2.45 ሰዓት የሚፈጅ በምስል የተደገፈ ቃለ መጠይቃቸው እንደሚያስረዳው በቤተክርስቲያን ምን ያህል የመናፍስት አሠራሩ ሥር እንደሰደደ አረጋግጠልናል።

ቤተክርስቲያን እጇን ተቆረጠች የተባለላቸው ሰው ራሳቸው ደመና ጠቅሶ ለመብረር የሚያስችል ድጋም እንዳላቸውና አብዛኞች ጓደኞቻቸው በዚህ ሥራ የተያዙ እንደሆነ መስክረዋል በእነዚህና መሰል ሰዎች እየተከተቡ ወደ ቤተክርስቲያን የሚገቡት መጻሕፍት ያለ ተቃዋሚ ለዘመናት ተሰግስገው በተጋረዱበት የግዕዝ ቋንቋና በቀለመ ደማቅ ሱቲ ተጠቅልለው ሲቀመጡ ቅዱስ ተብለው በየዕለቱ ይቆዩና ባልሰማነውና ባላወቅነው ልሳን ሲነበቡ የነበሩትን መጻሕፍት የያዘው ደብተራ እንድንሳለማቸውና እንድንተሻሻቸው ከምንጸልይበት የጸሎት ተመስጦ በቡጢም ይሁን በጸናጽል ድምጽ ይቀሰቅስና ግዴታውን እንድንፈጽምለት ከመደረጉ ባሻገር በመጸር (መስቀል የሚያዝበት እንጨት) ወይም በመቋሚያ በመድቃት ያባንነንና እርሱ የዕለት ግብሩን እንደፈጸመ ይቆጥረዋል:

ዘመን መጣ : ቋንቋ ዘመንና መቅደስ ምሽግ ሆኗቸው ሕዝቡን ሲገሉና ሲያስገድሉ የነበሩት የመከራ መጻሕፍቶቻችን እንደ ቀደመው ዘመን አወናብደው ላያልፉ ዕገሌ የተባልሁ ቅዱስ ነኝ ዕገሊት እባላለሁ ወይም ተአምር ዘዕገሌ ድርሳን ዘዕገሊት ገድለ እንትና እያሉ ማታለላቸው አከተመ።

ቀን ወጣ : ቁም ማን ነህ ? ወዴት ነው ? ከየት ነው ? ማን ላከህ ? ተመዘን ተለይ ሲባሉ ብርሃን ወጣ ። አሜን ። ሳናውቀውና ሳንረዳው ያጎነበስንላቸው እነዚያ ዛሬ ክብር ይሁንለትና ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ እንኳንስ ከእኛ ትከሻ ከሕዝባችን ትከሻ ለዘላለም ላይገኙ መረጃ ጠቅሰን ረድኤተ እግዚአብሔርን ይዘን አስተማሪ መንፈስ ቅዱስን አስቀድመን በጌታ ታምነን ልንገጥማቸው እግዚአብሔር አቆመን።

ለሰሚው ግራ፣ ለጸሐፊው ዕዳ፣ የሆነ ሃይማኖትን የሚያበላሽ ፣ቤተክርስቲያንን የሚያስነቅፍ፣ የሚያስንቅ፣ እግዚአብሔርን የሚያሰድብ፣ ለሰይጣን የሚያደላ፣ ርግማንን የሚያመጣ ጽሑፍ ተሸክመን እንደኖርን ጥቂቱን በዚህ መጽሐፍ ለመግለጥ ጀምረናል።

በእርግጥ የዚህ ኃላፊነት የአባቶቻችን ቢሆንም ምክንያታቸው በውል ባልታወቀ ሁኔታ ይደፍሩ ዘንድ እንዳልቻሉ ተመልክተናል። « የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ትጠብቋት ዘንድ እናንተን ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ » እንደተባሉ ብናውቅም እኛ ግን የሚጠበቅብንና የበኩላችንን ለማለት ደፍረናል።

ሳይሰሙ ቀርተው ነውን ? መጻሕፍቱን ሳያውቋቸው ቀርተው ነውን ? ክፉዎች ያደረጉትንስ ወንጀል ሳይረዱት ቀርተው ነውን ? የዓለም ቤዛ ነቢያትንና ሐዋርያትን ለመቤዤት ድንግል ማርያም ተወለደች ሰማይን በከዋክብት ምድርንም በአበባ ያስጌጠ ይህ መርቆሬዎስ ነው ፡ ታላላቅ ብርሃናትን ማለትም ፀሐይንና ጨረቃን የፈጠረች ድንግል ማርያም ናት ፡ ስለ ሰው ልጆች በመስቀል ላይ የተሰቀለው የሾህን አክሊል የደፋው መርቆሪዎስ ነው ፡ ፍጥረት ሁሉ እመቤታችንን ለማመስገን ተፈጠረ ፡ የተክለ ሃይማኖት ተቀማጥ ከክርስቶስ ደም ጋር አንድ ነው ወ.ዘ.ተ እየተባለ ከጽሑፍ አልፎ በየዕለቱና በየክብረ በዓላቱ በዜማ ሲንቆረቆር በውኑ ሳይታወቀ ቀርቶ ነውን ?

ዓላማችን የመናፍቃኑን ክሕደትና ወንጀል ደግመን ለመጻፍ ወደን ሳይሆን ባለማወቅ እየተነዳ ያለው ቁጥረ ብዙው ሕዝባችን የመጻሕፍቱንና የጸሐፊዎቻቸውን ጉድ ሰምቶና ተረድቶ ወደ ሕያውና እንከን ወደሌለበት ወደ እግዚአብሔር ቃል በበመለስ ለነፍሱ እረፍትና የዘላለም ሕይወትን ሊሰጠው ወደሚቻለው ጌታ ወደ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘወር እንዲል ለመርዳት ነው።

ይህ « ገድል ነው ገደል? » የተሰኘው መጽሐፍ ዋና ዓላማውም ሕዝቡ እስከ ዛሬ በሚያምናቸው አንዳንድ ካህናትና ሠራዊተ ዲያብሎሶች የተደረገበትን ወንጀል ተረድቶ ለወንጌል እሺ እንዲል ለማገዝ ነው።

ከዚህ በፊት በጻፍናቸው መጻሕፍቶቻችን ደጋግመን እንዳልነው ቤተ-ክርስቲያናችን የተተከለችበትን የወንጌል መሠረት ቀስ በቀስ እያስጣሏት ለመናፍስት አሠራር የዳረጓት ሰዎች የክፋት መሣሪያዎቻቸውን ጥለውና አቃጥለው እነርሱ ድነው ሕዝቡን እንዲያድኑ አልያም ቤተ-ክርስቲያናችንን

ለቀው እንዲወጡ ለማድረግ ሕዝባችንም በቀደሙትና በእውነተኞቹ አባቶቹ ትምህርት እንዲታደስ በነፍሳችን ተወራርደን መነሣታችንን በድጋሚ እናውጃለን

የተከበራችሁ አንባብያን እልክ ቅናትና ቂጭት እየተናነቀን ይህን ብለናል ስለሆነም በጽሑፉ ለሚፈጠር የቃል ግድፈት የአጻጻፍ ስልት ድክመት የጻፍንበትን ዓቢይ ዓላማ በመረዳት ታግሳችሁና አስተካክላችሁ እንድታነቡልን በማክበር እናሳስባለን ::

# ምዕራፍ አንድ

## መርቆሬዎስ
## እግዚአብሔርን የተካ ፈጣሪ

ዕገኒ ለስምከ ወእሴብሕ በኃይልከ ስምዓ ጸሎተ ኵሉ ዘሥጋ ዘመጽአ ኀቤከ ኢታኀንዲ እግዚኦ መርቆሬዎስ ሣህለከ በከዋክብት ሰማየ ዘከለልከ ወበጽጌያት ምድረ አሠርጎከ ፈኑ ብርሃነከ ወጽድቀከ እማንቱ ይምርሃኒ ወይሰዳኒ ደብረ መቅደስከ

/ጥቅምት 25 ገጽ 51 - 52/

የመጽሐፉ ደራሲ ፈጣሬ ዓለማት የሆነውን እግዚአብሔርን በመካድና በማስካድ የሰለጠነ መሆኑን ዓይኑን ጨፍኖ የጻፈውን ይህን የክሕደት መዝሙር እንይ:: ስሕተት የሌለበትና በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በቅዱሳን ሰዎች እጅ የተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ ከዋክብትን የፈጠረ፣ ምድርን በዕፀዋት ያስጌጠ፣ (ዘፍ 1÷9: 19) የሥጋ ለባሽን ሁሉ ጸሎት የሚሰማ ( መዝ 64÷ 1- 2 ) ብርሃንና እውነትን በመላክ ወደ ቅድስናው ተራራ የሚያደርስ ፍኖት(መንገድ) እግዚአብሔር እንደሆነ አስረግጦ ይናገራል::

ዚቅን ጽፈነዋል የሚሉት ውሉደ መናፍቃን ግን ሰው እንዳያውቅባቸው በግእዝ በሚያነበንቡት መዝሙራቸው ወደ አማርኛ ስንመልሰው እንዲህ ይነበብላቸዋል::

«ሰማይን በከዋክብት የሸፈንክ ፣ ምድርንም በዕፀዋት ወይም በአበቦች ያስጌጥህ መርቆሬዎስ ሆይ ለስምህ እገዛለሁ: በኃይልህም አመሰግንሃለሁ :ወደ አንተ የሚመጣውን የሥጋ ለባሽ ሁሉ ጸሎት ስማ ይቅርታህንም አታዘግይብን ብርሃንህንና እውነትህን ላክ እነርሱም ይምሩኝ ወደ ቅድስናህ ተራራና ወደ መቅደስህ ይውሰዱኝ » በማለት ጽፈዋል::

ምን እንዳሉ እንኳ ሳይረዳ ተንኮለኛ ዲያቆን ያነቃነቃትን ቃጭል እያዳመጠ እግዚአብሔር በእግሩ ወርዶ በፊቱ የቆመ ያህል እልል እያለ የሚሰግድላቸውን

የዋህ ሕዝብ በተሸፈነ ቋንቋ የአምልኮ ምንዝርናቸውን ከማለማመድ ባሻገር ሕዝቡ ባለማወቅም ቢሆን እየተራበው ያለውን ፍቅረ እግዚአብሔርና ጽድቅ እንዳያገኝ ወደ ንስሓም እንዳይመለስ በመርዝ ስብከታቸው በክሕደት ትምህርታቸው ተብትበው ይዘውታል።

ደራሴ ክደትና ወንጀል የሆኑት ጸሐፍተ ዚቅ መርቆሬዎስ እያሉ የሚጠሩት ሰው በ300 ዓመተ ምህረት ገደማ እንደነበር እንዳልጻፉ ሁሉ እርሱን ራሱን ወደዚህ ምድር ይመጣ ዘንድ በእናቱ ማሕፀን በሠራው በእግዚአብሔር ጥበበኛ እጅና የሥልጣን ቃል የተፈጠሩትን ፍጥረታት ይኸው መርቆሬዎስ ያሉት ሰው ነው የሠራቸው በማለት በልዑል ላይ ድፍረትን ተናግረዋል።

ለክሕደታቸው ጸጸት የማይታይባቸው እነዚሁ ጸሐፊዎች ኅዳር 25 ቀን ይህን ከላይ የተገለጠውን ዝማሬ ባለሟሎቹ ሲያሸበሽቡት መርቆሬዎስ የሚሉት ሰው በፈረስ ሆኖ በመገለጥ ከካህናቱ ጋር አብሮ ይታያል ይላሉ።

ካህናት ሁለት አይነት እንደሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል። አንደኛ የእግዚአብሔር ፤ ሁለተኛም የበዓል( የጣዖታት ) ። የጣዖታት ካህናት ለጣዖታቸው በሠሩት ቤት፣ በመዝሙርና በሥርዓት ያመልኩታል ይሰግዱለታል ይገዙለታልም። ምንም እንኳ የተሳሳቱ ቢሆንም የሚያደርጉት ሁሉ ለዚያው ለሚያመልኩት ጣዖት በመሆኑ ማድረግ ያለባቸውም ያንኑ ነው።

ካህናተ እግዚአብሔርም እንዲሁ ለሚያመልኩት ለሚገዙለት እውነተኛ አምላክ ለእርሱ የሚሆነውን ብቻ ያቀርባሉ። በተለይ እነዚህ በብሉይ ኪዳን የነበሩ የእግዚአብሔር ካህናት ለመሥዋዕታቸው ተጠንቅቀው እንደ ቅድስናው መጠን እርሱ ባሳያቸውና ባስተማራቸው ሥርዓት መሠረት እያመለኩ ሕዝብንም እያስተማሩ ሊያስመልኩት የተሾሙ ናቸው።

እነዚህ በእግዚአብሔር ቤት ላይ ተሹመው፣ ግን ለእግዚአብሔር ያልሆነውን ነውር ያለበትን የፍጡር አምልኮ መዝሙርና ቅዳሴ እያቀረቡ የእግዚአብሔርን ክሂሎት እየነጠቁ ለሟች ለፈራሽ ፍጡር እየሰጡ ያውም ለእግዚአብሔር ለብቻው የሆነውን የመፍጠር ባህርይ ወስደው «መርቆሬዎስ ሆይ አንተ ነህ ሰማያትን በከዋክብት የሸፈንህ፣ አንተ ነህ ምድርን በአበቦች ያስጌጥህ» እያሉ ራሳቸው ክደው ሕዝብን እያስካዱ ይገኛሉ።

ይህ መዝሙር ሲዘመርለት በፈረስ እየተገለጠ ያለው የእግዚአብሔር መልአክ ወይም እግዚአብሔር የላከው ሰው አልያም እነሱ እንዳሉት

በእግዚአብሔር ስም ቅዱስ ተብሎ የተጠራ ጻድቅ ሰው ሳይሆን ራሱን የብርሃን መልአክ በማድረግ እየለዋወጠ የሚገለጠውና የዚህን ዓለም የማያምኑ ሰዎች አዕምሮ ለማሳወር ጊዜው በሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር አሠራር እስኪታገድ ለጥቂት ጊዜ የተሰጠው ጠላታችን ሰይጣን እንደሆነ ለመረዳት አያስቸግርም ። ምክንያቱም የፈጣሪ ብቻ የሆነውን ባህርይ ያንተ ነው ሲሉት አዎ ብሎ የሚቀበል በክርስቶስ ደም የታጠበ ቅዱስ ሰው የለምና ።

## ስለ ሰዎች ልጆች ፍቅር የተሰቀለው መርቆሬዎስ ነው

ዜቅን ጽፈውታል የሚባሉት ሰዎች ሲያነቡ የተሳሳቱ አልያም የትምህርት ማነስ ምክንያት ሆኖ መንፈሳዊው ነገር ያልገባቸው ሳይሆኑ ሆን ተብሎ የእግዚአብሔርን ክብር ፣ የእግዚአብሔርን ምስጋናና የእግዚአብሔርን ሥራ በመለወጥ እንዲያገለግሉት ሰይጣን የሾማቸውና ራሳቸውም ለሰይጣን ያለጸጸት ለመገዛትና ለማገልገል የወሰኑ በርኩስ መንፈስ የተነዱ ናቸው።

በየዘመናቱ ተነሡ የተባሉት በርካታ መናፍቃን እንኳ ስለ ሰው ልጆች ኃጢአት የተሰቀለውና የሞተው እርሱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ አልካዱም። በባህርዩ ላይ ሕጸጽ ይገኝባቸው እንጂ ። አንዳንዶች ፍጡር ነው ፣ አንዳንዶችም ሁለት ባህርይ ነው ሌሎች ደግሞ አንድ ባህርይ ነው ቢሉም ስለሁላችን መከራን የተቀበለ የሞተና የተነሣው ክርስቶስ እንደሆነ ያምናሉ።

አገር በቀሎቹ የእኛዎች ከሐድያን ግን ሚያዝያ 25 ቀን በሚዜመው መዝሙራቸው ገጽ 170 ላይ እንዲህ በማለት ከእነቀያፋና ሐና የባሰውን ክሕደት ጽፈዋል።

«ንዜኑ ዘመርቆሬዎስ ሂሩተ ትኅትና
ወየውሐተ ዘተአገሰ በእንተ አፍቅሮተ
ሰብእ ዘሰቀሉ ለሰማይ ከመ ቀመር ዲበ
ዕፅ ተሰቅለ። ዘከለሉ ለሰማይ
በከዋክብት አክሊለ ዘሦክ ተቀጸለ»

ትርጉም:-

«ስለ ሰው ልጆች ፍቅር በመታገስ መከራን የተቀበለ በእንጨት ላይ የተሰቀለ ሰማይን እንደዋልታ የዘረጋና በከዋክብት የሸፈነ መርቆሬዎስ የሾኽ አክሊልን በራሱ ላይ ደፋ ስለዚህ ቸርነቱና ትኅትናው ደግነቱን እንናገራለን»

ኃጢአት ያስከተለውን በሥጋ ለባሽም ያልተቻለውን የኃጢአት ደመወዝ ( ዋጋ) ይኸውም ሞት ነው : መጽሐፍ እንደሚል እግዚአ ብሐር የገዛ ልጁን ልኮ አድርጎታል ይላል ( ሮሜ 8 ÷ 3-4 ) ኃጢአት ያስከተለውን ሞትና ከእግዚአብሔርም ክብር መጉደል እግዚአብሔር በራሱ ለመመለስ በመፍቀዱ ዓለም ሳይፈጠር በታቀደው መሠረት ርግማንን ያጠፋ ዘንድ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ተከቦ ይኖር የነበረው ኃያል አምላክ የሰላም አለቃ የዘላለም አባት ተብሎ የተጠራው ወልድ በተለየ አካሉ በሥጋ ሰብእ ተገልጦ ስለ ሁላችን በውክልና ለሞት ያውም ለመስቀል ሞት ተላልፎ እንደተሰጠ ራሱ ሰይጣን በግዱ ያመነው እውነት ነው::

ይህም በአብ ፈቃድ ስለመተላለፋችን እንደቆሰለ በደላችንንም እንደተሸከመ ( ኢሳ 53 ÷1-12 ) ነቢያት ተንብየውለታል :: አምላክ በሥጋ ተገልጦ በፈጠራቸው ሰዎች እጆች መከራን በመቀበል የሾኽን ጉንጉን አክሊል እያሉ ዓይኖቹን እየሸፈኑ ማን እንደመታህ ትንቢት ተናገር በማለት ሲቀልዱበት የሰው ልጆች ፍቅር ለዚህ እንዳደረሰው ደጋግ አበው ተናግረዋል:: መጻሕፍትም ገልጠዋል:: «ፍቅር ሰሐቦ ለወልድ እመንበሩ ወአብጽሖ እስከ ለሞት» ትርጉም «ፍቅር የአምላክን ልጅ ከዙፋኑ ሳበው እስከ ሞትም አበቃው» :: እንዲሉ::

ጸሐፍተ ዚቅ ወመዝሙር የሆኑት መናፍቃን ግን ከክርስቶስ ዕርገት በኋላ 300 ዓመታትን ቆይቶ ነበረ የተባለውን ፍጡር እንዲህ ብለውታል::

« ስለ ሰው ልጆች ፍቅር በመታገስ መከራን የተቀበለ በእንጨት ላይ የተሰቀለ ሰማይን እንደዋልታ የዘረጋና በከዋክብት የሸፈነ መርቆሬዎስ

የሾኽ አክሊልን በራሱ ላይ ደፋ ስለዚህ ቸርነቱና ትህትናው ደግነቱን እንናገራለን::» በማለት በድፍረት ጽፈዋል::

ወገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ የሚለውን የአሪት ዘልደት የመጀመሪያ ክፍል በመፋቅ « ሰማይን እንደዋልታ የዘረጋና በከዋክብት ያስጌጠ መርቀሬዎስ ነው » እያሉ በንባብም በዜማም እየደገሙ ከአንድ ኃይል አለ ባዩ ፍልስፍና በክሕደት የላቀውን ደረጃ አስመዝግበዋል::

ሰዎቹ መርቀሬዎስ እያሉ የሚጠሩትን ባዕድ መንፈስ አንዴ ፈጣሪ ዓለማት ሲሉት ሌላ ጊዜ ለሰው ልጆች ሲል የተሰቀለ ይሉታል :: የሚገርመው ፍጡር ሰው መሆኑን በድርሳናቸው መግለጣቸውን ረስተው ስግደትንና አምልኮን የሚቀበል አምላክ አድርገውም ስለውታል:: ዕድሜው ያልዘለቀውን ዕሩቅ ብዕሲ (ያውም በእርግጥ ኖሮ ከሆነ ነው ) እንዲህ እያሉ በቤተ-ክርስቲያን ሥፍራ ቢሰጡትም እኛ እግዚአብሔር ባቀደልን መሠረት ከድንግል ማርያም በእውነት በሥጋ በተገለጠው የእግዚአብሔር ልጅ በሆነው በክርስቶስ ከዛሬ 2000 ዓመታት በፊት በእንጨት ላይ ተሰቅሎ ባፈሰሰው ደሙ የኃጢአት ሥርዬትን እንዳገኘን የሲኦል መሠረቶች እስኪናጉ ድረስ እናውጃለን::

ጸሐፊዎቹ ክሕደታቸውን በዜማም ሆነ በስብከት ሀገር ያደረሰ ሥራ ክርስቶስን ተቀብያለሁ በማለት በስሙ ለተቋቋመችው ቤተ-ክርስቲያናችን ዛሬ ለምትገኝበት ዝብርቅርቅ ሕይወት እንድትወድቅ ዳርጓታል:: ግራና ቀኙን የማያውቀው ይህ ሕዝብ « አዕይንተ እግዚአብሔር » እያለ ካህናቱን ታምኖ የሚኖር በመሆኑ ሳይመረምርና ጥያቄ ሳያቀርብ ሁሉን ስለሚቀበላቸው ሳያውቀው እግዚአብሔርን እየተቃወመ ወደ ሲኦል እንዲነጉድ አድርገውታል::

ሌላው ቀርቶ በፍታታችን እናጸድቅሃለን የሚሉት እነኚሁ መናፍቃን በክርስቶስ ይሁን ወይም አይሁን የማይታወቅ አስከሬን በፊታቸው አጋድመው ምዕመኑ በማያውቀው ቋንቋ ከሚጸልዩት መዝሙር አንዱ « ሚስቱን ሌላ ይውሰዳት ልጆቹም ይበተኑ ሥልጣኑም ለሌላ ትሰጥ » የሚለውን በይሁዳ ላይ የተተነበየውን መርገም ነው :: ምን እንደተባለ የማያውቀው ሕዝብ አሜን በማለት ሲተባበራቸው ይታያል::

በእነዚህ የመናፍስት ቁርኝት አገልጋዮች ሤራ አብዛኛው የቤተ-ክርስቲያናችን አገልጋዮች ሳይቀሩ እንዳይቃወሙ ታሥረው በክፉዎች ትምህርት እየተነዱ ይገኛሉ:: የሚያሳዝነው በዓለ ስቅለት ዘክርስቶስ በደረሰ ጊዜ

« ዘበእንቲአሃ ለቤተ ክርስቲያን ተጸፋእከ በውስተ ዐውድ ከመ ትቀድሳ በደምከ ክቡር ዘበእንቲአሃ ዝግሐታተ መዋቅሕት ፆረ ወተዐገሠ ምራቀ ርኩስ እንዘ አልቦ ዘአበሰ አምላክ ዲበ ዕፀ መስቀል ተሰቅለ »

ትርጉም

« ለቤተክርስቲያን (ለማኅበረ- ምዕመናን) ስትል በአደባባይ በጥፊ የተመታህ አቤቱ ይህን ማድረግህ እርሷን በክበረ ደምህ ትቀድሳት ዘንድ ነው ለእርሷ ሲል ታሥሮ መጎተትን የቻለ የበደለውም በደል ሳይኖር ርኩስ ምራቅን ሲተፉበት የታገሠ አምላክ በእንጨት መስቀል ላይ ተሰቀለ » ( የያሬድ ጸሎት ) እያለች የምትዘምር ቤተ-ክርስቲያን ከፋዎቹ መርቆሬዎስ ሆይ ለሰው ልጆች ስትል በእንጨት ላይ ተሰቀልህ የእሾህም አክሊል ተሸከምህ የሚሉትን ውሉደ አጋንንት ለማገድ ተሸንፋ በክፉዎች ተወርሳ መታየቷ ነው::

## ኑ እንስገድላት ለርሷም እንገዛ

መቼም የዚቅ ጸሐፊዎች እንደ ሕንዳውያኑ እንደ ቻይናውያኑና እንደ ጃፓናውያኑ የአማልክት ችግር የለባቸውም:: ደስ ያላቸውን ምድርን ሠራህ ሲሉት ደስ ያላቸውን ደግሞ ሰማይን ፈጠርህ ይሉታል :: ከፈለጉም ጨረቃን የሠራህልን አንተ ነህ፣ ደግሞም ለአዳም ኃጢአት ዋጋ የከፈልህ አንተ ነህ በማለት ጠርተን የማንጨርሰው ፣ቆጥረን የማንፈጽመው ስያሜ እየሰጡ ይሾሙታል::

በዚህ በዚቅ መጽሐፍ በየካቲት 16 ንባብ ገጽ 144 ላይ « ንዑ ንስግድ ወንግነይ ላቲ ለመድኃኒትነ ማርያም ድንግል ለዘገብረት ብርሃናተ ዓበይተ ባሕቲታ » የሚል ጽሑፍ ይገኛል::

በቤተ-ክርስቲያኒቱ ተሰግስገው የሚገኙት እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን ለማስቀናት ታጥቀው የተነሡ በመሆናቸው በመሰሎቻቸው ዘንድ በግልጽ እንደሚታወቀው ከሰይጣን ጋር በሚያደርጉት ቃል ኪዳን ተዋርሶ ካደረጉ በኋላ ሌሎችንም በዚህ ወጥመድ ለመጣል እነርሱ ጥበብ የሚሉትን ምክረ ዲያብሎስ በቤተ-ክርስቲያኒቱ ሥርዓቶች በመሸፈን የዋሑን ሕዝብ ጭምር ለኃጢአታቸው ተባባሪ ያደርጉታል::

በዚህም ጽሑፋቸው « ንዑ ንስግድ ወንግነይ ላቲ » ማለትም « ኑ እንስገድላት እንገዛላትም » በማለት ለአምልኮ ክሕደታቸው ጥሪ ያቀርባሉ:: ስለ

እግዚአብሔር ግብሮች ጠንቅቀው የሚያውቁቱ እነዚህ ሰዎች ለእግዚአብሔር የሆነውን ሁሉ ለወደዱት በማደል :- ኢታምልክ ባዕደ አምላክ ዘእንበሌየ. .. እያለ ቀናተኛው አምላክ (ዘፀ 20÷1) እነ ይሉኝታ እርሙ ግን አብሾ ባዞረው ጎሊና ሥራሥር ባጠዘው አዕምሮ « ንዑ ንስግድ ወንግነይ ላቲ » በማለት ድፍረት ተናግረዋል:: ይህን የመናፍቃን ድርሰት የዛሬ 2000 ዓመት ገደማ ሰይጣን እጅግ ይናፍቀው እንደነበር ማቴ 4÷8-9 መመልከት በቂ ነው ::

ለሰከንድ ለምትደረግ ስግደት ሰይጣን ሊከፍለው ያዘጋጀውን ክፍያ የመንግሥታትን ክብርና ሀብት ነበር:: መምህራችን ክርስቶስ ግን « ሂድ አንተ ሰይጣን ለአምላክህ ብቻ ስገድ ተብሏል » በማለት ያሳፈረውን ከሐድያኑ ግን ዛሬ ደስ ላላቸው መንፈስ ሁሉ አምልኮ፣ ውዳሴ፣ ስግደት፣ መገዛት ይገባናል እያሉ በጌታችን ያጣውን ምኞት ያረኩታል

> « <u>ወኢትግበር ለከ አምላከ ዘበውስተ ሰማይ በላዕሉ ወዘውስተ ምድር በታሕቱ ወዘበውስተ ማያት ዘበታሕቲሃ ለምድር ኢትስግድ ሎሙ ወኢታምልኮሙ</u> » ትርጉም « <u>በላይ በሰማይ ካለው በታችም በምድር ካለው ነገር ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ አትስገድላቸውም</u> » ( ዘጸ 20 ÷ 4 )

የሚለውን አምላካዊ ትዕዛዝ በመጣስ የሰው እጆች በሳሉት ሥዕል ፊት በመቆምና በማስቆም ስግደት እንዲደረግ ይሰብካሉ::

መጽሐፍ « <u>ወዝኒ አኮ ለአንክሮ እስመ ለሊሁ ሰይጣን ይትሜሰል ከመ መልአከ ብርሃን</u> » ትርጉም « <u>ሰይጣን ራሱ የብርሃን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣል</u> » እንደሚል ( 2ኛ ቆሮ 11 ÷ 14 ) መምሰል የሰይጣን ዋነኛ ባሕርዩ በመሆኑ በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናት በቅድስት ድንግል ማርያም ስም በማመሳሰል ኑ እንስገድላት እንገዛላትም በማለት ይጋብዛሉ ::

በመሠረቱ ጌታችንን መድኃኒታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን መድኃኒት አድርጎ የተቀበለ ሰው ለማን እንደሚሰገድ ለምን እንደሚሰግድ ስለሚያውቅ በፈጣሪ ፈንታ ስግደትን በራሱ ስም ይቀበል ዘንድ አይችልም አያደርገውምም :: መናፍቃኑ ለጌታችን እናት ነው በሚል ሽፋን ስግደት እንስጣት ያሏት ሴት

የጌታችን የመድኃኒታችን እናት አለመሆኗ ደራሲዎቹ ቀጥሎ በጻፉት መዝሙር በግልጽ ይታወቃል::« ሰማያትን በከዋክብት ያስጌጠልህ መርቆሬዎስ ነው ሲሉን ቆይተው አሁን ደግሞ « ብቻዋን ታላላቅ ብርሃናትን ለፈጠረች ለመድኀኒታችን ለድንግል ማርያም ኑ እንስገድላት ለእርሷም እንገዛ ... » ይላሉ::

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ትኅትናዋ፣ ስለድንግልናዋ፣ በእግዚአብሔር ፊትም ስለተቀበለችው ሞገስ የመሰከረላት እመ ለእግዚእነ ( ማርያም ) በሕይወት ኖራ ቢሆንና ይህን የመናፍቃንን ክፉ ሥራ ማለትም ያላለችውን ፣ ያልፈለገችውንና የማትፈልገውን የፈጣሪ ተግዳሮት ብትሰማ እንዴት ታዝን እንዴትስ ትከፋ ?

የተወደደችው የጌታችንና የመድኃኒታችን በሥጋ እናቱ የሆነችው ድንግል ማርያም እንዲህ ያለውን የመናፍቃን ሤራ ተባባሪ ያለመሆኗን በመዝሙሯ ስትገልጽ እንዲህ ብላለች:: « ታዐብዮ ነፍስየ ለእግዚአብሔር ወትትሐሠይ መንፈስየ በአምላኪየ ወመድኀንየ ትርጉም « ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች » (ሉቃ 1÷ 46-47)

መጽሐፍ ቅዱሳችንን ስንገልጽ የመጀመሪያው የዘፍጥረት መጽሐፍ ዓለማትንና በውስጣቸው ያለውን ማንኛውንም ፍጥረት እም ኀበ አልቦ ኀበ ቦ ያመጣው የአብርሃም ፣የይስሐቅ፣ የያዕቆብ አምላክ እግዚአብሔር እንደሆነ ያውጃል:: ( ዘፍ 1: 1 - 31 )

እግዚአብሔር በስድስት ቀናት ውስጥ ፍጥረታትን ሁሉ «ይሁን» በማለት በሚያወጣው የሥልጣን ቃል እንደፈጠራቸው ይታወቃል:: በተለይ በዘፍ 1÷ 14 - 19 « ወገብረ እግዚአብሔር ክልኤተ ብርሃናተ ዐበይተ ዘየዐቢ ብርሃን ከመ ይምልክ መዓልተ ወዘይንዕስ ብርሃን ከመ ይምልክ ሌሊተ ምስለ ከዋክብት » ትርጉም « ቀንና ሌሊትን ይለዩ ዘንድ ብርሃናትን በሰማይ ጠፈር ይሆኑ ለምልክቶቹም ለዘመናችም ለዕለታት ለዓመታትም ይሆኑ በምድር ላይ ያበሩ ዘንድ በሰማይ ጠፈር ብርሃናት ይሁኑ እንዲሁም ሆነ :: እግዚአብሔር ሁለት ታላላቅ ብርሃናትን አደረገ:: ትልቁ ብርሃን በቀን እንዲሰለጥን ትንሹም ብርሃን በሌሊት እንዲሰለጥን ከዋክብትንም አደረገ:: በምድር ላይ ያበሩ ዘንድ በሰማይ ጠፈር አኖራቸው :: በማለት ይናገራል::

ፈጣሪ ዓለማት ልዑል እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ይሰጡት ዘንድ ያላቸውን አገልግሎትና ችሎታ የመኖሪያ ሥፍራ በክሂሎቱ ሰጥቶ እንዲኖሩ እስከ

ቀጠረላቸው ቀን ድረስ ሥራቸውን በሚገባ እየሠሩ ይታዩ ዘንድ ፀሐይን፣ጨረቃንና ከዋክብትን እንደፈጠረ ቅዱስ ቃሉ እየገለጸ የመጽሐፈ ዚቅ ወመዝሙር ደራሲዎች ግን « ታላላቅ ብርሃናትን የፈጠረች ድንግል ማርያም ናት » በማለት የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ አራተኛ አካል አድርገው ይዘምራሉ :: ለነገሩ ለማርያምና ለመስቀል(ለእንጨቱ) የመለኮት ክብር ይገባቸዋል በክብር ተካክለዋልና በማለት በእነ ዘርዓያዕቆብ ዘመን ታውጆ የለ?

ጸሐፊዎቹ « ማርያም» እያሉ የሚጠሯት መጽሐፍ ቅዱስ ስለትኅትናዋ፣ ስለቅድስናዋ፣ ስለታማኝነቷ፣ እግዚአብሔርን ስለመፍራቷ የጻፈላትን የጌታችንን እናት ማርያም ነች ለማለት አንደፍርም::

መጽሐፍ ቅዱስ ማርያም እያለ የሚጠራት እንኳንስ የሥላሴን ክብር ልትሻማ ቀርቶ በሥጋ ከእርሷ የተገለጠውን ልጇን በእናትነቱ ልኩራ ሳትል « ጌታዩ አምላኬ » ብላ የነፍሷ መድኃኒት እንደሆነ እንጂ እኔ መድኃኒት ፣ፈጣሪ ነኝ አላለችም:: ምናልባት ጸሐፊዎቹ ማርያም ያሏት በሩቅ ምሥራቅ የምትመለከው « የሰማይ ንግሥት » የሚሏትን ይሆን ?

ደራሲዎቹ ማርያም የሚሏትን ሴት « መድኃኒታችን » በማለት ይጠሯታል:: ቅን ልብ ላለው በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠችውንና መልአኩ ገብርኤል ወደ እርሷ ተልዕኮ ስለመጽነሷና ስለመውለዷ ያበሠራት ቅድስት ማርያም በየትኛውም ሥፍራ « የጌታችን እናት » እንጂ መድኃኒት ናት ተብሎ አልተነገረላትም::

ሐዋርያት « በሰማይም ሆነ በምድር ሌላ የምንድንበት ( መድኃኒት የሚሆን) ስም የለንም (ሐዋ4፥12) እያሉ አበውም በመጽሐፋቸው « ድኅነታችን በዕሩቅ ብዕሲ » አይደለም እንዲህ ብሎ የሚያምን ርጉም ነው ብለው ጽፈው እያለ( ሃይማኖተ አበው ) መናፍቃኑ ግን « ማርያም የተባለችው « መድኃኒታችን ናት በማለት ያዜማሉ::

## ነቢያትንና ጻድቃንን የምትዋጅ ማርያም ናት

በዚቅ መጽሐፍ ገጽ 174 ላይ « ከመ ትቤዙ ነቢያተ ወጻድቃነ አማን ተወልደት ... ማርያም »:: <u>ትርጉም</u>:- ነቢያትንና ጻድቃንን ትዋጅ ዘንድ ማርያም በእውነት ተወለደች » ይላል:

ይህን የከሐዲዎች መጽሐፍ ለመጻፍ እንዲህ አሉ በማለት ያነሣሣን በመግቢያችን ላይ እንደገለጥነው ሕዝባችን በክፉዎች ሥራ ምን ያህል እንደተያዘና ወደ ክርስቶስም ለማምጣት ምን ያህል ሥራ እንዳለብን ለማሳየት እንጂ በእነርሱ የተባለውንና የምንጠላውን ወንጀል ደግመን ለመጻፍ ወደን አይደለም

ጸሐፊዎቹ ታጥቀው የተነሡት እግዚአብሔር ቀስ በቀስ ከሕዝቡ ኅሊና እንዲፋቅ ያ ካልሆነም ለእግዚአብሔር ለብቻው የሆነውን ባሕርያትና ግብር ለፍጡራትና በፍጥረታቸው ለማይታወቁ መናፍስት በመስጠት ፍጡራትን ከእግዚአብሔር ጋር ማስተካከል ወይም በሕዝቡ አእምሮ በእግዚአብሔር ምትክ ፍጡራትን መተካት ነው።

አዲስ ኪዳን ከሚያተኩርባቸው የክርስቶስ የጌታችን ብቻ ግብር የሆኑትን በመንጠቅ ደስ ላላቸው ሁሉ እያከፋፈሉ የክርስቶስን ውለታ ለማስረሳት ወደር ያልተገኘለት ሥራ ሠርተዋል። ይህም ተሳክቶላቸው ዛሬ በሰፊው ምዕመን ዘንድ 30ዎቹ ቀናትና መጻሕፍት ባሳደሩት ተጽዕኖ ከክርስቶስ ይልቅ ማርያም፣ ገብርኤል፣ ተክልየ፣ አቡየ፣ ወ.ዘ.ተ የተሻሉና የቀረቡ ረዳት እየተባሉ ይታወቃሉ ያታመናሉ ፡

የዚቁ ደራሲዎች « ከመ ትቤዞ ነቢያተ ወጻድቃነ » ብለው ማርያም ተወለደች ። በማለት የደስታ ያህል ሊያበሥሩን ሞክረዋል። ነቢያትንና ጻድቃንን ለመቤዠት ማርያም በመወለዷ ለምስጋና ጠርተውናል ።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኃጢአትና ውጤቱ ሲናገር « <u>እስመ ኲሎሙ አበሱ ወኀጥዑ ወኀደጉ ስብሐተ እግዚአብሔር</u> » ትርጉም « <u>ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሏቸዋል</u> » ( ሮሜ 3÷23 ) ይላል። ከዚህ የተነሣ ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ በመሆኑ ከእግዚአብሔር ተለይቶ እንደሚኖርና እንደኖረ ያስረዳናል፡ ሆኖም ባለ ብዙ ምሕረት እግዚአብሔር ይህን በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር ክብር ጎድሎ የነበረውን የሰው ልጅ ለማዳን ያዘጋጀውን እቅዱን ሐዋርያቱ ሲገልጡ « <u>ወጽድቅሰ በከንቱ ኮነ በጸጋ ዚአሁ ረከቡ ሕይወተ በኢየሱስ ክርስቶስ</u> » ትርጉም «... <u>ነገር ግን በክርስቶስ በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ</u> » ብለው መሰከሩ ። ( ሮሜ 3÷24)

በክርስቶስ ቤዛነት እንጂ በሌላ በማንም ቤዛነት በኩል አልተባለም። ወይም ግማሹን በክርስቶስ ቀሪውን ደግሞ ዛሬ የእኛዎቹ መናፍቃን እንደለቀለቁት

በዕገሌ በኩል ይቻላል እያሉ እንደሚያስተምሩት በአንዱ ስንኳ ይቻላል አላሉም::

ቤዛነት : ማለት በግዕዙ ቤዘወ ከሚለው ግሥ የወጣ ሲሆን ዋጀ ፣ገዛ ማለት ነው: ቤዛነት ስንልም ዋጅነት ወይም ቤዛ መሆን ተብሎ ይተረጎማል:: ይህንም ሥራ እግዚአብሔር ለተወደደ ልጁ ብቻ እንደሰጠው ለዚህም ሥራ በተለየ አካሉ ወልድ በሥጋ ተገልጦ እንደፈጸመው ቅዱሳት መጻሕፍት ይተባበራሉ::

ሐዋርያው ጴጥሮስ በመጀመሪያው መልእክቱ « አላ በክቡር ደሙ ለክርስቶስ ከመ ዘበግዕ ቅድው ወንጹሕ » ትርጉም « በክቡር በክርስቶስ ደም እንደተዋጃችሁ ታውቃላችሁ » ይላል: በቅዱስ ጴጥሮስ ትምህርት መሠረት ለቤዛነቱ ባለቤት ሆኖ የተገለጠው « መድኃኒታችን ክርስቶስ ብቻ ነው » ( 1ኛ ጴጥ 1÷ 19)

ቅዱስ ጳውሎስም በኤፌ ክታቡ 1÷7 ላይ « ረከብነ መድኃኒተ ወተኀድገ ኀጢአትነ በደሙ » ትርጉም « በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን » በማለት የቤዛነቱን ሥራ ደሙን ባፈሰሰው በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ እንደሆነ መስክሯል:: « በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም » ሲል ( ተቤዥታ ችኋል፣ ተዋጅታችኋል ) ማለቱም ነው:: ( 1ኛቆሮ 6÷20 )

ጥቅል የመቤዠታችንን ነገር ቅዱስ ጳውሎስ በሐዋርያት ሥራ ለተሰባሰቡ ጳጳሳት ( የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ) ሲያስረዳ « እግዚአብሔር በደሙ የዋጃትን ቤተክርስቲያን (የምዕመናን አንድነት ) ትጠብቁ ዘንድ ... በማለት በዚህ ሥራ ማንም ጣልቃ ይገባ ዘንድ እንዳልፈቀደ ባለቤትነቱን « እግዚአብሔር በገዛ ደሙ የዋጃትን » በሚል ኃይለ ቃል ተናግሯል ( የሐዋ 20÷ 28 ) በተለይ ግዕዙ « ቤተክርስቲያነ ለክርስቶስ እንተ አጥረያ በደሙ » በማለት በክርስቶስ ደም የነጻች የሚለውን ትርጉም ሰጥቶታል::

ታዲያ የመጽሐፈ ዚቅ ደራስያን ነን ባዮች « ማርያም የተወለደችው ነቢያትን ጻድቃንን ለመቤዠት ነው » ሲሉ ያሠፈሩትን ተግዳሮት ከየት አመጡት ? በሥጋ ከእርሷ የተወለደው ክርስቶስም የመስኮታዊ ግብሩ ተካፋይ እንደሆነች የገለጠው ያስተማረውና የተናገረው የለም :: እንዲያውም « አባቴ ይሠራል እኔም ደግሞ እሠራለሁ » ሲል እናቴም ደግሞ የእኛን ሥራ

ትሠራለች አላለም (ዮሐ 5፥ 17 ) በእኔም እመኑ በአባቴም ደግሞ እመኑ ሲል » በእናቴም ደግሞ እንዲሁ አላለም:: ( ዮሐ 14፥ 1-3 )

ክርስቶስ በአባቱ በመንፈስ ቅዱስና በራሱ ፈቃድ ( በአሐቲ የመለኮት ፈቃድ) በሥጋ ወደ ምድር ሲመጣ ነቢያትንና የዚቅ ደራስያን ጻድቃን እያሉ የሚጠሯቸውን ደራሲዎቹ እንደሚሉት ማርያም የተቀረውን ሕዝብ ደግሞ ክርስቶስ እንዲቤዣቸው በሚል አይደለም:: « ሁሉም ኃጢአትን ስላደረጉ የእግዚአብሔርም ክብር ስለጎደላቸው በእርሱ ቤዛነት በኩል ብቻ እንዲጸድቁ ዓለም ሳይፈጠር እግዚአብሔር በወሰነው መሠረት ነው::

በዚሁ መጽሐፋቸው ገጽ 65 ላይ « የዓለም ሁሉ ቤዛ የሆነች ማርያም » በማለት ጽፈዋል:: የጸሐፊዎቹ ዓላማ በግልጽ እንደሚታየው የእግዚአብሔርን የቸርነት ሥራ ማጥፋት መሰወር ስለሆነ « የዓለም ቤዛ» ብለው እንዲዘምሩላት ለዚህች ሴት መዝሙር ደርሰዋል::

እግዚአብሔር ዓለሙን በክርስቶስ ቤዛነት ሊያድን እንደፈቀደና ይህም ኃሳቡ ከዘመናት ጀምሮ ነቢያት በትንቢታቸው፣ ሐዋርያት በስብከታቸው ፣ ተተኪ ልጆቻቸው በጽሑፋቸው፣ቀደምት የተባሉትም በትውፊታቸው እስከ ነፍሳቸው ሕቅታ መስክረው ያለፉለትን በመካድ « ማርያም ቤዛዊተ ኩሉ ዓለም( የዓለም ሁሉ ቤዛ ) ፣ብኪ ንድኅን ወነሐዩ (ባንቺ እንድናለን እንኖርማለን) በማለት በክርስቶስ መድረክ ያውጁታል::

__በእነርሱ አባባል__ :-

1. ታላላቅ ብርሃናትን ( ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት) የፈጠረች ማርያም ናት
2. እነርሱ ማርያም የሚሏት ለሕዝብ መድኃኒት ናት ( እውነተኛይቱ የጌታችን በሥጋ እናቱ ማርያም አይደለችም )
3. እነርሱ ማርያም እያሉ ለሚጠሩአትም እንስገድላት ለእርሷም እንገዛ ማለታቸው ነው ::

የሚገርመው ጸሐፊዎቹ ፈጣሪ፣ መድኃኒት፣ ቤዛ፣ አዳኝ፣ መመኪያ፣ መጋቢ፣ ጠባቂ ወ.ዘ.ተ ማለት ችግር የለባቸውም:: ቁጥራቸው ቢበዛም አይጨንቃቸውም:: ብዙዎች እንደሚመስላቸው ሰዎቹ የማርያም ፍቅር አላስችላቸው ያላቸው መስሏቸው « ፍቅረ ማርያም » ነው እያሉ

ከንፈራቸውን መጠውላቸዋል ። እንበልና የማርያም ፍቅር ነው ብንል እንኳ ሰዎቹ በማርያም ፍቅር ብቻ የሚረኩ አይደሉም።

በዚሁ መጽሐፋቸው ገጽ 80 ላይ « መርቆሬዎስ ወከነ መድኃኒተ ለኩሉ ዘነፍስ » ትርጉም « መርቆሬዎስ ለፍጥረት ነፍስ ሁሉ መድኃኒት ሆነ » ይላሉ። እንደገናም የዚህ የዚቅ መጽሐፍ ወንድም የሆነው ገድለ ተክለ ሃይማኖት ደግሞ :-

« ዝንቱ አቡነ መምህርነ ዝንቱ ፍርቃንነ ዝንቱ ተስፋነ ዝንቱ ግዕዛንነ ዝንቱ አብ ክዳን ለእርቃንነ፣ መብልዓ ለጽድቀ ረኃብነ፣ ስቴ ሕይወት ለጽምዕነ ምርጉዝ ለድካምነ

ይህ አባታችን ይህ መድኃኒታችን ይህ አለኝታችን ይህ ነፃ አድራጊያችን ይህ የመንግሥተ ሰማያት ፈለማችን በታረዝን ጊዜ ልብሳችን በተራብን ጊዜ እውነተኛ ምግባችን በተጠማን ጊዜ የሕይወት መጠጣችን በደከምን ጊዜ ምርኩዛችን »

ይላል( ገድለ ተክለ ሃይማኖት ገጽ 10 ምዕ2÷16 )

(ዝርዝሩን በምዕራፉ እናየዋለን)

እንደደራሲዎቹ ኃሳብ ይህ አባታችን ( ተክለ ሃይማኖት ) መድኃኒታችን ነው በማለት ይሰብኩናል። ማርያም ቤዛዊተ ኩሉ ዓለም ብሎ የዓለም መድኃኒት እንደሆነች የተናገሩትን ረስተው መርቆሬዎስ ወከነ መድኃኒተ ለኩሉ ነፍስ ብለውን ነበር። ብዙ መድኃኒት ብዙ አዳኝ ለጸሐፊዎቹ ችግር ስላይደለ አሁን ደግሞ ተክለ ሃይማኖት መድኃኒታችን በማለት ጽፈው ሕዝቡን አስተውታል ። ሐዋርያት « የዓለም መድኃኒት እንዲሆን አብ አንድያ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታል » ( 1ኛ ዮሐ 4÷ 14 ) ያሉትን በመካድና በማስካድ ስልጥነዋል።